ግንቦት, 2012 (ወርሀዊ) ቅንነት ድል ያደርጋል! ESQUAREADVERTISING

# ቅንዴል DIGITAL MAGAZINE

KENDEL DIGITAL MAGAZINE 2ND EDITION




## "...ኢትዮጲያዊነት ለኔ ክብሬ ነው!..."


ቅፅ-፪ ቁጥር-፪

እውን ኮሮና የላብራቶሪ ስሪት ነው?
✍ ዞስ-ካለስ

‹‹የዘመን ቁጭት የግዜው ተስፋ አባይ››
✍ በሀይሉ ወ/ይፍራው

በኮሮና ወቅት ሊወሰዱ የሚገቡ 5ስነልቦናዊ እርምጃዎች
✍ ፍራኦል መስፍን

# ማውጫ




**01** ርዕሰ-አንቀፅ

**02** የዘመን ቁጭት
የጊዜው ተስፋ አባይ
**ሀገሬ**
በሀይሉ ወንድይፍራው

**08** የአውደብሩሀን ገፆች
ቆይታ ከራሄል ጌቱ ጋር

**13** የቅኖች ገፅ

**15** ሁለት እውነት አለን!
**አጻኢብ**
በነዒል አቡበከር

**20** በኮሮና ወቅት ሊወሰዱ
የሚገባቸው 5ስነልቦናዊ
እርምጃዎች
**አዕምሮ ጤና**
በፊራኦል መስፍን

**25** ለምን ላግባ
**ንንሳ አወት**
በአናናስ ግርማይ

**27** እልፍ ገፆች
በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ

**28** የጤና ባለሙያዎች እና
ህመማቸው
**ትዝብት**
በ ቀለዮጳ ደስታ


**32** የቤተሰብ ወግ
በ ገላና ጥጉ

**33** እውን ኮሮና የላብራቶሪ
ስሪት ነው?
**ሳይ-ቴክ**
በ ዞስ ካለስ

ቅንድል
DIGITAL MAGAZINE

# ቅንጅል መፅሔት

# 1ኛ አመት







ከሀሳባውያን ማጀት ወጥተን ወደ ተግባራውያን ዕልፍኝ ከተሸጋገርን እነሆ አንድ አመት አስቆጠርን።
የቅንድል ዲጂታል መፅሔት አንባቢያን እና ቤተሰቦች ያለ እናንተ ማበረታት እና ድጋፍ አንድም እርምጃ
መራመድ አንችልም ነበር። እናንተ ለሰጠችሁን በዋጋ ለማይታመነው የቅንነት ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን።
ለመጪው ትውልድ የሚጠፉበትን ቂም ፣ ዘረኝነት ፣ አለማወቅ እና እራስ ወዳድነት ከማውረስ ይልቅ
የሚኖሩበትን እውቀት ፣ ፍቅር ፣ አንድነት ፣ ሀገር ፍቅር እና ምክንያታዊነት እናውርስ።
ቅን እና መልካም ሆነን ከተዋደድን በፍቅር የማይሸነፍ የለም!
ኑ የቅኖች ፣ የምክንያታዊና ሀገር ወዳድ ትውልድ እልፍኝ ወደ ሆነው ቅን-ድል ኢትዮጲያ የወጣቶች ህብረት
ይቀላቀሉ።

ቅን እናስባለን ፣ ቅን እናወራለን ፣ ቅን እንሰራለን!!!

# ርዕሰ- አንቀፅ

## ችግሮቻችንን ለሠናይ ምግባር

ኣለማችን ሁኔታው እና መጠናቸው ይለያይ እንጂ በየጊዜው የተለያዩ ችግሮችን አስተናግዳለች ፣ አሁንም እያስተናገደች ትገኛለች ፣ ወደ ፊትም ማስተናገዷን ትቀጥላለች።
ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ በመፈለግ ታዲያ የሰው ልጆች ሲታትሩ፣ ደግሞም አዳዲስ የመፍትሔ ሀሳቦችን እና ግኝቶችን ሲያገኙ ማየት የተለመደ ነው። አብዛኛዎቹ ዛሬ ላይ የምናያቸው እና የምንጠቀምባቸው የፈጠራ ውጤቶች ታድያ መነሻቸው ዓለማችን በዘመናት መካከል ያስተናገደቻቸው ችግሮች ናቸው። "ብዙዎቹ የፈጠራ ውጤቶች የችግር ልጆች ናቸው።"
ለምሳሌ ቶማስ ኤድሰን ማብራትን(አንፖልን) የፈጠረው ጨለማ በጣም ያስፈራው ስለነበር ነው።
ሌላ ምሳሌ ልጨምርላችሁ። ወንድሙን በደም ካንሰር ህመም ምክንያት ያጣው የላፕሮጋዳ ሱባሮው በመማር እና በመመራመር አሚኖ ፒተሪን የተባለውን የደም ካንሰር መድሀኒት ሊያገኝ ችሏል።
በአሁኑ ጊዜ የመላው ዓለም ስጋት የሆነው ኮቪድ-19 ትልቁ የጊዜው ችግር መሆኑ እሙን ነው። ይህንንም ተከትሎ የተለያዩ የመንግስት እና የግል ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ መዝናኛ ቦታዎች፣ የሀይማኖት ተቋማት እና ሌሎችም በመዘጋታቸው ብዙዎችን ለችግር፣ አንዳንዶቹን ለስራ ማጣት ሌሎችን ደግሞ በሽታውን ተከትሎ ለሚመጡ መሰል በርካታ ችግሮች ተዳርገዋል።
በመሆኑም በዚህ ፈታኝ ወቅት ሁላችንም ራሳችንን እና ወገኖቻችንን ከ ኮቪድ-19 እየጠበቅን ይሄንን በሽታ እና በሽታውን ተከትለው የመጡትን ችግሮች ከችግሮቻቸው ባሻገር ማየት እና ችግሮቹን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ለችግሮቻችን መፍትሔ በማበጀት ቅድም ካነሳናቸው ታሪክ ሁሌም ከሚያስታውሳቸው ትልልቅ ሰዎች መሀል አንዱ መሆን እንችላለን። ለዚህም ራሳችንን ወደ ውስጥ በማየትና ያለንን ዕምቅ ሀይል እና ችሎታ በማውጣት ለራሳችን፣ ለቤተሰቦቻችን፣ ለሀገራችን ብሎም ለምድራችን የበኩላችንን በማበርከት ችግሮቻችንን ለሠናይ ምግባር እንጠቀም የዛሬው መልዕክታችን ነው። ሰላም!

ቅንድል ዲጂታል መፅሔት በቅንድል ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ማህበር ወጣቶች ተዘጋጅቶ በ E-SQUARE አድቨርታይዚንግ እና ኢቨንትስ የሚቀርብ በማህበራዊ፡ ስነልቦናዊ እና ጤና ነክ ጉዳዮች ዙርያ የሚያተኩር ዲጂታል መፅሔት ነው።
የካቲት 2011 ተቋቋመ።
✔ አድራሻ
✆(+251)912178520
✆(+251)920019699

E-MAIL- KDIGITALMAGAZINE@GMAIL.COM
TELEGRAM- @KENDELM
FACEBOOK- ቅንድል ዲጂታል መፅሔት
WWW.ETHIOKINDEL.COM

- ቀለዮጳ ደስታ
e-mail-cleopadada2012@gmail.com
Telegram- @adadada8
✆(+251)941535884

✔ማኔጂንግ ዳይሬክተር- ኤርሚያስ ደጀኔ
e-mail- ermiyasdejene@gmail.com
telegram- @jeremy00
✆(+251)912178520

✔ም/አዘጋጅ
- ነፃነት ጌታቸው
e-mail:- netsanetg43@gmail.coment
telegram- @mistretigist
✆(+251)953498678

✔ከቨር ኢሉስትሬሽን & ሌይ አውት ዲዛይን- MHgraphics
e-mail- EsruMh1@gmail.com
Telegram- @EsruMH
✆(+251)920019699

✔አዘጋጆች
- በሀይሉ ወ/ይፍራው ( መባ)
e-mail- ethiomebreku3000@gmail.com
telegram- @dasolo
✆(+251)924140293


✔አርት ዳይሬክተር- ፍራኦል መስፍን
e-mail:- firaolmesfin8@gmail.com
telegram- @forgiven247
✆(+251)923602445

✔ማርኬቲንግ - ያሬድ ለማ
e-mail- Yaredlemma487@gmail.com
Telegram- @Yared4444
✆(+251)932540523

-ነዋል አቡበከር
e-mail- newalabubeker13@gmail.com
telegram- @entisar13
✆(+251)937683378

✔አርታኢ - አወት ሀይለስላሴ
e-mail- awoth12@gmail.com
telegram- @awicha12
✆(+251)920152581

-ዮናስ ኃ/ማርቆስ
e-mail- lijyoha2@gmail.com
Telegram- @Yonas_H
✆(+251)970514616



በበሀይሉ ወ/ይፍራው( መግ)
በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የማኔጅመንት መምህር
በዘነሰ ሪሰርቸር
ethiomebreku3000@gmail.com



# የዘመን ቁጭት የጊዜው ተስፋ አባይ

*የግዮን መገኛ÷ ግሽ ተራራ ምንጩ
ኢዳባልቆ ሚሄደ÷ ጥቁር እና ንጩ
ሀገር እንዳ ለንም÷ በአንድ ልብ ያሰረ
ከእውነት የገጠረ÷ ከእውቀት የጠጠረ
አባይ የህይወት ውሀ÷ ከደም የወፈረ።*

ተፈጥሮ ለሰው ልጆች ከለገሰቻቸው ዕልፍ ትሩፋቶች መሃል ብቻም ሳይሆን በሀይማኖታዊ አስትምህሮ ውኃ የሰው ልጅ የተሰራበት አንዱ ግብዓትም ነው። ምን አልባት አለም ስትሰራ፣ ተፈጥሮ አዳልታ የለገሰችው ብዙ የሚባሉ የዘመን ስጦታዎች አሉ፤ 'ከነዚህ ውስጥ ትልቁ ማነው ካላችሁኝ' አባይ ነው መልሴ።

ሰላም ውድ የሀገሬ አምድ አንባቢያን እና የቅን-ድል ቤተሰቦች እንደምን ከርማችኋል ሳምንቶቻችሁን በቅንነት እና በምክንያታዊነት እንዳሳለፋችሁ እምነቴ ነው። በዛሬው የሀገሬ አምድ ለዘመናት ከቁጭት እስከ ተስፋ የዘለቀውን ፣ ሁሉን ኢትዮጲያዊ እኩል ስሜታዊ የሚያደርገውን እና የወቅቱ የሀገራችን ብሎም የአለም ፖለቲካ መዘወሪያ ስለሆነው አባይ በጥቂቱ ለማየት ወደድኩ።

ታላቁ ወንዝ አባይ በቁጭትም በአድናቆትም ከጭስ አባይ አርሶ አደር እስከ ግብጽ ነጋዴ ብዙ ተብሎለታል። ታዲያ ይህ ታላቅ የተፈጥሮ ስጦታን አለም እንደ ቅኔ ለመፍታት ዘመናትን ሲኳትን የኖረው ምን ድብቅ እና ውስብስብ ነገር ቢኖረው ነው?
አባይ በሀገራችን የጥንት ድርሳናት ብቻ ሳይሆን በታላቁ መጽሀፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 10 እስከ 13 እንዲህ ሲል ይገልጸዋል " ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔደን ይወጣ ነበር ፤ ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር። የአንደኛው ወንዝ ስም ፊሶን (ፊሾን) ነው ፣ እርሱም ወርቅ የሚገኝበትን የኤውላጥ ምድርን ይከብባል...... የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው ፤ እርሱም የኢትዮጲያን ምድር ሁሉ ይከብባል::" በማለት በመጽሀፍ ቅዱስ ተከትቦ እናገኛለን። ታዲያ ይህ ታላቅ ወንዝ በተለያዩ ማህበረሰቦች የተለያዩ ስያሜዎች ተሰጥቶት እናገኛለን፡

ከነዚህ ውስጥም ለዘመናት አባይ ሲፈስ እና ከደጁ ሲመነጭ ያየው የጥቁር አባይ ማህበረሰብ ግዮን ሲለው ፤ ቀሪዎቹ የሀገራችን ህዝቦች ደግሞ አባይ ብለው ሲጠሩት ፣ የዚህ ታላቅ ወንዝ ተፈጥሮ ተቋዳሽ በመሆን የዘለቁት ሱዳኖች ደግሞ ‹‹ አልባስራቅ›› ብለው ሰይመውታል፤ ለዘመናት አባይን በብቸኝነት ስትጠቀም የኖረችው የሰሜን አፍሪካዊቷ ግብጽ ህዝቦች ‹‹ኢተሩ ወይም ታላቁ ወንዝ›› ሲሉ ያደረገላቸውን ታላቅ ስጦታ ይናገራሉ።

በሌላ በኩል የስልጣኔ ቀደምት፣ የዲሞክራሲ ፋና ወጊ የሆኑት ግሪኮች ደግሞ ‹‹ ኤሮስ ወይም የሸለቆ ወንዝ በማለት ይጠሩታል። ይህ ስመ ብዙ ፣ የግብጾች የህልውና መሰረት ፣ የሀገራችን የዘመናት ቁጭት የጊዜው ተስፋ፣ የጠቢባን የዜማ ምንጭ፣ የድርሳናት የብዕር ቀለም የሆነው አባይ ተነግሮ የማያልቅ፣ ተጽፎ የማይበቃ ፣ ፈሶ የማይደርቅ ትሩፋት አለው።

የቀደምት ግብጻውያን የዘመን አቆጣጠር ቀመር  ከአባይ ወንዝ መሙላት እና መጉደል ጋር እንደሚያያዝ አንዳንድ የታሪክ መዝገቦች ያሰፍራሉ። በዚህ ብቻ ያላበቃው የአባይ እንቆቅልሽ በርካታ  የአለም ሀገራትን እና አሳሾችን ቀልብ ለመግዛት ችሏል። ብዙ አሳሾች እና የአለም ሀገራት የታላቁን የአባይ ወንዝ መነሻ ለማወቅ እና የያዘውን እንቆቅልሽ ለመፍታት ብዙ ደክመዋል። ከ400 አመታት በፊት ወደ ሀገራችን የመጡት አውሮፓውያን የክርስትና እምነትን ከማስፋፋት በዘለለ የታላቁን የአባይ ወንዝ መነሻ ለማወቅ ብዙ ጥናቶችን እና ስለላዎችን እንዳከናወኑ የታሪክ ምሁራን ያስረዳሉ። ነገር ግን ብዙዎቹ የዚህን ወንዝ ሚስጥር ለዘመናት መፍታት አልቻሉም ነበር።

 ታዲያ አንድ ከስኮትላንድ ንጉሳውያን ቤተሰብ የሚወለደው ጀምስ ብሩስ የተባለ ግለሰብ  ያካሄደው ጥናት ለብዙ የዘርፉ ተመራማሪዎች እና አውሮፓውያን አሳሾች የመነሻ ሀሳብ የሚሆን ግኝት ማሳካት ችሎ እንደነበር ይነገራል። ጀምስ ብሩስ የአባይን መነሻ የማወቅ ጉጉቱ ከፍተኛ ስለነበር በህዳር 10 1768 እ.እ.አ ወደ ኢትዮጲያ በመምጣት ከምጽዋ ወደ ጎንደር አቅንቶ ለሁለት አመታት የግዕዝ እና የአማርኛን ቋንቋ በማጥናት የወቅቱን የሀገራችንን ንጉስ አጼ ተክለሀይማኖት ሁለተኛ በማስፈቀድ ጥቅምት 28 1770 እ.እ.አ ወደ አባይ መነሻ በመሄድ ምርምሩን አከናውኗል።

 አስቡት አውሮፓውያን የሌሎችን ታሪክ እና የተፈጥሮ ጸጋ ለማጥናት ይህን ያህል መስዋትነት እና ቁርጠኝነት ሲያሳዩ  እኛ የራሳችንን ባህል ፣ ወግ ፣ ቅርስ እና ስጦታ በመግፋት እርስ በርስ ያልኖርንበት ታሪክ ላይ የበላይነት እና ተበዳይነትን ለማንገስ ሰርክ እንፋተጋን ፣ እንዋቀሳለን፣ እንካሰሳለን። ይህን የራሳችንን የማጠልሸት አዚም በተመለከተ ወደ ጽሑፌ ማጠቃለያ ላይ ሀሳብ እሰጥበታለሁ፤ ወደ ጀምስ ብሩስ የአባይ ወንዝ መነሻ ግኝት እንመለስ።

የአባይ ወንዝ መነሻ በተለምዶ የግዩን ምንጭ መፍለቂያ ተብሎ የሚጠራው ግሽ ተራራ እንደሚሆን ጀምስ ብሩስ ሀሳቡን እንዳሰፈረ ጥንት ድርሳናት ያስረዳሉ። ይህ የግሽ ተራራ የሚገኘው በምዕራብ ጎጃም ሰከላ ወረዳ ግሼ አባይ ከተማ በስተ ደቡብ አቅጣጫ ነው፡ ግሽ ተራራ ከባህር ወለል በላይ 3180ሜትር ከፍታ እንዳለው ይገመታል።



አባይ ወንዝ በሀገራችን ከዘመን የህዝቦች ቁጭትነት እስከ አዝማሪ ቤት ብሶት የሆነ ታላቅ ወንዝ ነው። ስለዚህ ወንዝ ከታላቁ ባለ ቅኔ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን ግጥም ጀምሮ እንጋፋ ሙዚቀኞች ድረስ ተዘፍኖለታል። ታዲያ ለም አፈሩን ጠራርጎ ይዞበት ሲሄድ የታዘበው የሀገሬ ገበሬ እንዲህ ሲል በቁጭት ገጥሞለታል፦

‹‹ አባይ ነፍሰ ገዳይ፥ መሄድህን እንጂ መውሰድህን አታይ ››

በዚህ ያላበቃው የአባይ ቁጭት እና ብሶት ባለዋሸንቱን አፍቃሪ የሀገሬ እረኛ አባይ ሞልቶ የሀገሩን ወዝ ይዞ ምድሩን እያስራበ ባዕድ እንደሚያጠግብ የተረዳ ግዜ ፣ ፍቅሩን በአባይ መሄድ እና መምጣት አስታኮ ህልም ሲያይ እንዲህ ሲል አስገጥሞታል፡

‹‹ እረ ነይ እረ ነይ፥ እረ ነይ በመስኩ
የአባይማ ነገር፥ አልታወቀም ልኩ››
‹‹ የአባይ ውሀ ሞልቶ፥ ይፈሳል ቦይ ለቦይ
ምነው በህልሜ መጣሽ፥ ደህና አይደለሽም ወይ ››

አባይ ለገበሬው ብሶት ፣ ለአፍቃሪው ህልም ሆኖ ሲኖር፣ ዘመን ተቆጥሮ ዘመን ተክቶ ያየ የሰሜኑ የሀገሬ አቀንቃኝ ርእሶም ገ/ገርግስ ‹‹ ታ ዓባይ ነፋሪት ›› ብሎ አዚሞለታል።

ይህ የብዙ አመታት ብሶት እና ቁጭት ፣ ዘወትር እሱን እያየ የሚኖረውን የጥቁር አባይ ፣ የቤንሻንጉል ጉባ ነዋሪ ገበሬ ዛሬም ድረስ እራቱንም ፣ ጥናቱንም በኩራዝ እንዲያደርግ ፈርዶበት ኖሯል ሲሉ ብዙዎች ሀሳባቸውን ያቀርባሉ። ለኔ ግን እውነታው ከዚህ እንደሚለይ የገባኝ ተዋዳጇ አቀንቃኝ እጅጋየው ሽባባው (ጂጂ) እንዲህ ስትል አባይን በግርምት ስትዘፈነው ነው።

‹‹ የማያረጅ ውበት፥ የማያልቅ ቁንጅና
የማይደረቅ የማይነጥፍ፥ ለዘመን የፀና
ግርማ ሞገስ……… አባይ
የሀገር ጸጋ የሀገር ነፍስ ›› ይህ ዜማ አባይ ለኛ ሲሳይ እንጂ መርገምት እንዳልነበረ ያስረዳል። አዎ አሁንም ድረስ የሀገራችን ህዝብ ከአለም ተነጥሎ በኩራዝ ያበራል በእንጨት ይጋግራል ግን ይህ የሆነው አባይን ለዘመናት ስናይ የነበረው፣ በዘፈን አይን እንጂ በህልው አይን ስላልነበረ ነው። አፈር እየገፋ ባዕድ ሲመግብ እና የሀገር ብሶት ሆኖ የነበረው አባይ እኛ ከዘፈን የዘለለ ትርጉም ስላሰጠነው እንጂ አሁን ላይ እንደጀመርነው ተገድቦ ቢሆን ከ ሩብ ሚሊዮን ህዝብ በላይ ከድህነት ወጥቶ ኑሮውን በአባይ ላይ ይመሰርት ነበር። ስለዚህ አባይ በዘመናት የእርስ በእርስ ትግላችን እና ለእውቀት በሰጠነው ያነሰ ግምት እና ከዘፈን ያለፈ አይን ስላልጣልንበት እንጂ ባይተዋር አድርጎ ከፈለቀበት መሬት ይልቅ ባዕድ መርጦ ሄዶ አይደለም። በ2003 ዓ.ም በግብጽ የተጀመረውን የሁስኒ ሙባረክ መንግስት ተቃውሞ ምክንያት አድርጎ በወቅቱ የሀገራችን መሪ አቶ መለስ ዜናዊ የተጀመረው የታላቁ የህዳሴ ግድብ በብዙ ውዝግቦች መሀል ለሀገራችን ተስፋ ፣ ለግብጽ እና ሱዳን ስጋት ሆኖ እነሆ እዚህ ደርሷል። አሁን ላይ ሀገራችን ኢትዮጲያ ከመቼውም ጊዜ በላይ አንድነት እና የጋራ ትብብር የምትሻበት ወቅት ነው። ምክንያቱም መቶ ሚሊዮን ህዝቧን የሚመግብላትን እና ከ 1.8 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የሚያስገኝላትን የአባይ ውሀ ግብጽ እንደቀልድ አትመለከተውም። የትኛውንም አማራጭ ተጠቅመው ይህንን ግድብ ማስተጓጓል ይፈልጋሉ። አሁን ሁሉም ኢትዮጲያዊ ለ11 ተፋሰስ ሀገራት በተፈጥሮ የቀረበውን አባይ እኩል መጠቀም እንደሚገባን በማመን ውስጣዊ ሽኩቻችንን፣ የቋንቋ እና የሰፈር ፀባችንን ትተን፣ ወገባቸውን አጉብጠው ከጫካ ቅጠል እየለቀሙ አይናቸው በጭስ እየጠፋ ልጆቻቸውን ለሚመግቡ ሚሊዮን እናቶች ብሎም ከኩራዝ ወደ መብራት ለመጠቀም ለሚጠብቀን እልፍ ህዝባችን ስንል መተባበር እና እያንዳንዱን ነገር በትኩረት ማየት ይገባናል።

ይህ ውሀ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት ገጸ በረከት ነውና እኛ አንድ ሆነን የሚገባንን በመውሰድ፣ የማይገባንን በመስጠት ሀገርኛ አስተሳሰብን ብሎም የሰው ልጅ መገኛ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ አሳቢ መሆናችንን እናስመስክር እያልኩ የዛሬው የሀገሬ አምድ ጽሁፌን በዚሁ አበቃሁ። በቀጣይ በሌላ ርዕስ እስከምንገናኝ በቅንነት ፣ በመልካምነት እና በሀገር ፍቅር እያንዳንዱን ቀን እንድታሳልፉ እየተመኘሁ በቴዎድሮስ አበበ ግጥም ተሰናበትኩ።

<u>የእረኛው ትዝብት</u>

ከኢትዮጲያ ምድር፥ እንዲፈልቅ የጠራው
አሳምሮ ፈጥሮ፥ እግዚአብሔር የሰራው
አፈሯን ሸርሽሮ፥ ለሌለው ቢሰጥም
ድንበሯን አቋርጦ፥ ሌላውን ቢያጠግብም
የአባይን ልጅ ውሀ፥ ሲጠማው ቢደንቅም
‹ለምን ሆነ? › ብዬ፥ አማርሬ አላውቅም
ታዲያ…..
የሀገሬን ወንዝ ውሀ፥ የገዛ ንብረቴን
ብገድብ ፣ ብጠቀም፥ ባለማ መሬቴን
ዛቻ፣ ማስፈራሪያ ፥ ቁጣን ምን አመጣው
አምላክ የሰጠኝን፥ ብቀዳው ፣ ብጠጣው!

እንደ ህዝብ ስንረዳዳ እንደ ሀገር እንቆማለን ፤ እንደ ሀገር ስንቆም ታሪክ እንሰራለን!!!
‹‹ መልካም እና ሰላማዊ ሆነን ከተዋደድን በፍቅር የማይመለስ የለም ››
ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር……….





ታምራት ታደሰ ደነቀ
የትምህርት ጥራት አማካሪና አሰልጣኝ
email:-Addisayer@gmail.com



# አዕምሮን መመገብ

# ወይስ? ሆድን መሙላት

ትኩረትና ቅድሚያ መስጠት ያለብን ለየትኛው ነው?

በአንድ አጋጣሚ ለንደን ከተማ መሃል በሚገኘው ትልቅ አደባባይ እስራኤላውያን በሚያከብሩት በዓል ላይ ተገኝቼ ሳለሁ አንድ በዕድሜው ከ55 የዘለለ፣ ሰውነቱ ፈርጠም ያለ ይሁዳዊ አገኘሁና ስለ በዓሉ ሁኔታ እንዲሁም ስለ ግል ህይወቱ መነጋገር ጀመርን። ሁልጊዜ መጠየቅና ከሰዎች የህይወት ልምድ መማርና ማወቅ ስለምፈልግ ትዳር እንዳለውና ሌላም ሙያ ነክ ጥያቄዎቼን በአርጋታና በማስተዋል አንድ በአንድ ጠየቅሁት። ለሁሉም ጥያቄዬ መልሰ ቢመልስልኝም በአሁኑ ሰዓት ብዙውን መልሴን የረሳሁት ሲሆን የአንድ ጥያቄዬ መልስ ግን እስከዛሬ ድረስ እንቅልፍ ነስቶ እየረበሸኝ በልቤ ቀርቷል። የዚህ የአንድ ጥያቄ መልስ ነው እኔንና ሃገሬን፤ ህብረተሰቤን አኗኗሬን አስተሳሰቤንም ጭምር መለስ ብዬ እንድፈትሽ ያስገደደኝ። ምልልሳችንም እንዲህ ነበር ፡ -

ጥያቄ፡ - ልጆች አሉህ
መልስ፡ - አዎን አሉኝ
ጥያቄ፡ - ስንት ልጆች አሉህ
መልስ፡ - ሁለት ልጆች አሉኝ (አንድ ወንድ አንድ ሴት)።
ጥያቄ፡ - እንዴት በዚያን ጥሩ ጊዜ ሁለት ለጆች ብቻ ወለድክ
መልስ፡ - ሆዳቸውን ብቻ አልነበረም የምሞላው አዕምሮአቸውንም መመገብ ነበረብኝ። ለዚህ ደግሞ በቂ ዝግጅት ያስፈልጋል "ልጅ እኮ በዕቅድ እንጂ በዕድል ያድጋል ተብሎ አይወለድም" አለኝ። ትንሽ ግራ ተጋብቼ በዝምታ ለሴኮንዶች ከቆየሁ በኋላ 'ዓሣ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል' እንደሚባለው ቀጥዬ ሌላ ጥያቄ አቀረብኩ።
ጥያቄ፡ - 'አሁን ልጆችህ ምን ይሠራሉ አልኩት?' ምክንያቱም አዕምሮአቸውን እመግብ ነበር ስላለኝ ማወቅ ጓጉቼ።
መልስ፡ - ወንዱ ልጄ የሕግ ባለሙያና ዓለም ዓቀፍ ጠበቃ ነው ሴቷ ደግሞ የህክምና ባለሙያና የትልቅ ሆስፒታል ሬጂስትራር (ዋና አስተዳዳሪ ናት) ሲለኝ ሰውየውን ሳይሆን ያየሁት 'እራሴን የት ነው? ያለሁት ምን እየሰራሁ ነው?' በማለት መጠየቅ ጀመርኩ። በመቀጠል 'ለመሆኑ ልጆችህ ትዳር ይዘዋል?' ብዬ ጠየቅሁት እርሱም 'አዎን' በማለት 'ሁለቱም ሁለት ሁለት ልጆች እንደወለዱና ደስተኛም ኑሮ' እንደሚኖሩ አብራርቶ ገለፀልኝ።

ከዚያማ ምኑን ልጨብጠው አስተዳደጌን፣ የተማርኩትን ትምህርት፣ ያደግሁበትን ባህልና ህብረተሰባችን፤ ስለልጅ ያለውን አመለካከት፣ የወላጆች የልጅ አያያዝ፣ በልጆች ላይ የሚደርሱ የአካል፣ የስነልቦና፣ የወሲብና የመገለል ጥቃቶች፣ በእያንደንዱ ቤተሰብ የልጆች ቁጥር ብዛት፣ አባቱን የማያውቅ ልጅ ብዛት፣ የተጣሉና የተረሱ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃናት፣ በገጠር በእረኝነትና ለከባድ ሥራ የተጋለጡ፣ ህይወታቸውም በዚያ ተወስኖ የሚቀሩ ህፃናት፣ በለጋ ዕድሜያቸው በየሜዳውና በየመንገድ ዳር የእናቶቻቸውን የቀሚስ ጫፍ ይዘው በፀሐይና በሐሩር፣ በዝናብና በብርድ የሚንገላቱና መለመኛ የሆኑ..... ብቻ ስንቱን ልቁጠረው። በተጨማሪ በመካከለኛው ምሥራቅ በአፍሪካና በዓለም ሃገራት በስደትና በእንግልት የተበተነው ወጣት ሁሉም በአንድ ጊዜ በአዕምሮዬ መጡ፤ መንፈሴም ተረበሸ፤ ባዶነትም ተሰማኝ፣ የምደገፍበትም አጣሁ፤ የቆምኩበትም መሬት የከዳኝ መሰለኝ። እራሴንም ሃገሬንም ያለሁበትንና የምሠራውን እያወጣሁና እያወረድኩ በሃሳብ ቆዝሜና አንገቴን ደፍቼ፣ ሰውዬውን ተሰናብቼ ወደ ቤቴ አመራሁ።

በሃገራችን በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ በከተማና በገጠር በሚቸገርበት፤ የሃላፊነት ስሜት በማይሰማቸው ወላጆች የሚወለዱና በእንክብካቤ የማያድጉ ህፃናት በበዛበት፤ ሌትና ቀን እንኳ ተሰርቶ በማያልፍ የድህነት ችግርና ሥራ ፈት መንገዱንና ሠፈሩን በሞላበት ሃገር ስንቶቻችን ይህን አውቀንና አስተውለን ለመለወጥ ተዘጋጅተናል?

ከላይ የጠቀስኩት ችግር መንስኤ ለመረዳት ይረዳ ዘንድ ገጠመኞቼን ላጫወታችሁ። በአንድ አጋጣሚ በሚኒ ባስ ተሳፍሬ ስጓዝ ዕደሜዋ 30 የምትጠጋ ሴት ከአጠገቤ መጥታ ተቀመጠች፣ እኔም እንደ ለማዴ ከሰላምታ በኋላ ስለሥራዋ መጠየቅ ጀመርኩ።

መልሷም የጉልት ነጋዴ መሆኗንና በኑሮ ውድነት እንደተቸገረች፣ በተጨማሪ በልቧም ያለውን ብሶቷንም ሆነ ደስታዋን፣ ዕቅድዋንም ሆነ ሃሳቧን አጫወተችኝ። ከታክሲው ከመዉረዷ በፊት ግን እንድ የመጨረሻ ጥያቄ ጠየኳት።
"ኑሮ እንዲህ ከባድ ነው። ቀኑን ሙሉ ደክመሽ ከእጅ ወደ አፍ ብቻ ነው የምታገኚው። ዕድሜሽም እየገፋ፣ ጉልበትሺም እየደከመ ነው፤ ለመሆኑ ልጅ ወልደሻል ወይ፣" ብዬ ብጠይቃት አልወለድኩም ስትለኝ እኔ ደግሞ መልሼ መዉለድ ታስቢያለሽ ብላት አፍታም ሳትቆይ "እራሴን ሳልተካማ አልሞትም" አለችኝ። የዕርሷ ኑሮ ማጠፊያው አጥሮ በየጉልቱ ስትንከራተት በቂ የሆነ መጠለያና ምግብ እንኳ ሳታገኝ ሌላ ነፍስ ወደዚህ ዓለም ለማምጣት ያላት የሃሳበ ጽናት ገርሞኝ ዝም አልኩ።

በሌላ አጋጣሚ አንድ በሹፍርና የሚሰራ ሰው ጥሩ ገቢ እንዳለውና የሁለት ልጆች አባት እንደሆነ፣ ልጆቹ ስለሚበሉትና ስለሚኖሩበት ብዙም እንደማይጨነቅ በኩራት ካጫወተኝ በኋላ ትንሽ ገንዘብ ካገኘ ደግሞ ሌሎች ሁለት ልጆች ጨምሮ እንደሚወልድ ያለዉን የወደፊት ሃሳብ ገለፀልኝ። ሁሉን ካዳመጥኩ በኋላ ሁለት ጥያቄዎች አቀረብኩለት "ምናልባት በአንድ አጋጣሚ አንድ ችግር ቢያጋጥምህና መሥራት ባትችል ገቢም ባይኖርህ ልጆችህን ምን ታበላለህ ?" ነበር ወዲያው የመለሰልኝ መልስ "ፈጣሪ ያውቃል" ነበር። ከመልሱ የተረዳሁት ግን የራስንና የፈጣሪን ድርሻ ጠንቅቆ ካለማወቅ ስለሆነ አዘንኩ ። ሁለተኛዉ ጥያቄዬ ደግሞ "ለልጆችህ መፅሐፍ ገዝተህና አንብበህ ታውቃለህ ወይ?" ነበር።

መልሷ ግን "በፍፁም" ነበር። እዚህ ላይ አዕምሮ መመገብና ሆድን መሙላት ልዩነቱ በግልፅ ታየኝ። የአብዛኛዉ የሃገራችን ልጅ አወላለድና አስተዳደግ ሆድን በመሙላት ዙሪያ የሚያጠነጥን ስለመሆኑ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

እንግዲህ ሃብታም የሚባሉት ሀገራት አንድ ወይም ሁለት ቢበዛ ሶስት እየወለዱ፣ ልጆች ነገ ትልቅ ቦታ ደርሰው ሃገር ተረካቢ እንዲሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሲያሳድጉ፣ እኛ ደግሞ በፈጣሪ እያሳበብን እንደፈለግን እየወለድን ትውልድ በስደት ተበትኖ በባህር መስመጥ፣ በአውሬ መበላት፣ በኮንቴይነር ታፈኖ መሞት፣ በሰው ሃገር በእስር መንገላታት፣ ክብርን ማጣት በሃገር ውስጥ ደግሞ ተስፋ የቆረጠ፣ በትምህርቱ ደካማ ጥሩ የሥራ ባህል የሌለው፣ በተለያየ ተፅዕኖ የታሰረ፣ ቁጥሩ የበዛ ሥራ ፈትና አቅጣጫውን ማየት የማይችል ትውልድ ማፍራት ሆኗል ሥራችን። በቅርቡ የዓለም ባንክ ባወጣዉ ዘገባ ከአፍሪካ በህዝብ ብዛት ሁለተኛ የሆነችውን ግብፅን ባላት ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ምክንያት ኢኮኖሚያዋ በከፍተኛ ሁኔታ ሊናጋ እንደሚችል አስጠንቅቋል።

በተመሳሳይ ያለ ቤተሰብ ዕቅድና ያለ ሃሳብ ተወልዶና አድጎ ለሥራ የደረሰን የሃገራችንን 12 ሚሊዮን ለሚጠጋ ሥራ ፈላጊ፣ መንግሥት በሃላፊነት የሥራ ዕድልን እፈጥራለሁ ብሎ ከአቅሙ በላይ ከሚታገል፣ ‘እውነቱን ተናግሮ እመሽበት ማደር’ እንደሚባለዉ ግማሹ ሃላፊነት ‘ልጅ በእድሉ ያድጋል’ እያለ ልጆችን ወደዚህ ዓለም ያመጣውንና እንዲቸገሩ ያደረገውን ወላጅ ተጠያቂ ማድረግ አለበት።

በአጠቃላይ ኢኮኖሚዉ ባደገበት፣ ኢንደስትሪው በተስፋፋበት፣ የወጣት ሃይል ብዙ ጠቀሜታ ቢኖረውም፣ ገና ባላደገ ሃገር ግን ‘ሰፊ የወጣት ሃይል ለኢኮኖሚው ትልቅ ሃይል ነው’ እየተባለ እራስን ማታለል እንዳይሆን ከቻይና የአንድ ልጅ ፖሊስ በመማር አወላለዳችን ተመጥኖ፣ የልጆችን ሆድ መሙላት ብቻ ሳይሆን አዕምሮአቸውን መመገብና አቅም ያለው ጠንካራ ዜጋ መፍጠር የሁላችንም ሃላፊነት መሆን አለበት።

በተጨማሪ በሃገራችን የስነ ህዝብ ምጣኔ ከሃገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ለማጣጣም ያስችለን ዘንድ መንግሥት ከሃይማኖት መሪዎችና ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን በዚህ ሃገራዊ ችግር ላይ በተለያየ የመገናኛ ብዙሃን መነጋገርና መሰረታዊ ግንዛቤን ለህብረተሰቡ ማስጨበጥ ይኖርበታል። አለበለዚያ ግን ሥራ ፈት ወጣት ይበዛና፣ ከተጠበቀውና ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ ያይልና አሁን ከምናያቸው እዚህና እዛ ከሚፈጠሩ ትናንሽ ችግሮች የበለጠ ሃገራችንን ለከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ እንዳያጋልጣት ከወዲሁ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማሳሳብ እወዳለሁ።

---




**የሀዘን መግለጫ**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪ በነበረችው ተማሪ ሃይማኖት በዳዳ ሕልፈተ ሕይወት የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ዝግጅት ክፍል የተሰማንን ልባዊ ሐዘን እየገለፅን ለተማሪ ሃይማኖት በዳዳ ወላጆች፤ ቤተሰቦች እና ለኮሌጁ ማህበረሰብ በሙሉ መፅናናትን እንመኛለን።
በሴቶች ላይ የሚደርሱት መሰል ጥቃቶች ፍፁም ተቀባይነት የሌላቸውና የምናወግዘው መሆኑን የቅንድል ዲጂታል መፅሔት የዝግጅት ክፍል ይገልፃል።



# ቆይታ ከራሄል ጌቱ ጋር

በነፃነት ጌታቸው

ሰላም ውድ የአውደ - ብሩኃን ገጾች አንባቢያን እንደምን ቆያችሁን? እንደሚታወቀው የአውደ - ብሩኃን ገጽች አምድ ላይ በሀገራችን በተለያዩ የሙያ መስክ በመሰማራት ለሀገራቸው መልካም የሚባሉ ትሩፋቶችን ያበረከቱ ግለሰቦች እና በመዝናኛው፣ በትምህርት፣ በቢዝነስ፣ በስፖርት ፣ በኪነ-ጥበብ  እና በሌሎች መስኮች በሰሯቸው ተግባራት ለወጣቶች አርአያ የሚሆኑ እና ለአንባቢያንን እያዝናኑ የህይወት ስንቅ ያስይዛሉ ያልናቸውን እንግዶች የምናቀርብበት መድረክ ነው።  የዛሬው የአውደ - ብሩኃን ገፆች እንግዳችን ሙዚቀኛ ራሄል ጌቱ ስትሆን ብዙዎቻችን ‘በየእኛ’ የቡድን ስራ የምናውቃት እና ከቅርብ ግዜ ወዲህ በተለያዩ ነጠላ ዜማዎችን በመስራት ተወዳጅነትን አትርፋለች። ታዲያ ራሄል ጌቱን የመጽሄታችን እንግዳ ስናደርግ ለእናተ አንባብያን እና አድናቂዎቿ ከህይወት ተሞክሯዋ ባለፈ ከሙዚቃዋ ስኬት ጀርባ ያሳለፈችውን ጥረት እና ጥንካሬ ትማሩበታላችሁ ብለን በማሰብ ነው። በመሆኑም ሙዚቀኛ ራሄል ጌቱ ከቅን-ድል መጽሄት ጋር ያደረገችው ቆይታ በአውደ - ብሩኃን ገፆች አዘጋጅ ነጻነት ጌታቸው እንደሚከተለው ይቀርባል።
ሰናይ ንባብ!

**ቅንደል**፦ በመጀመሪያ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት እንግዳዬ ለመሆን ፍቃደኛ ስለሆንሽ በቅንድል መፅሔት አዘጋጆችና አንባቢያን ስም ከልብ እመሰግናለሁ።
**ራሄል**፦እኔም እንግዳችሁ አድርጋችሁ አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር ያክብርልኝ።
**ቅንደል**፦ወደ ጥያቄዎቻችን ከመግባታችን በፊት እኔ ከማስተዋውቅሽ አንቺው ለአንባቢዎች እራስሽን አስተዋውቂልን።
**ራሄል**፦ (ትንሽ ሳቅ) እሺ። ራሄል ጌቱ እባላለሁ። ሙዚቀኛ ነኝ
**ቅንደል**፦ እስቲ ወደ መጀመሪያው ጥያቄ በቀጥታ ላምራ እና ከቡድን ውጪ ስንት ሲንግል ሙዚቃዎችን ሰራሽ? ከሰራሻቸው በጣም የምትወጅውና ገልፆኛል የምትይው የትኛው ነው?
**ራሄል**፦ እእእ አራት ሲንግሎችን ሰርቼ ለቅቂያለሁ። የመጀመሪያዬ “ጥሎብኝ” ነው። ከዛ በኋላ “እልጓጓም” ፣ ከወዳጄ ወንዴ ማክ ጋር “ፋሽን ነው” የመጨረሻው ደሞ ባለፈው ሳምንት የተለቀቀው “የሀገሬ ሰው” አራተኛ ስራዬ ነው። ለኔ ሁሉም ጥሩ ናቸው ብዬ አምናለሁ ያው አድማጭም እንደወደደው ስላየሁ። እንደ አንድ ሙዚቀኛ ከመጀመሪያም ሙዚቃዎቼን ስሰራ ይገልጸኛል ብዬ አምኜበት ነው።



**<u>ቅንደቤ</u>**፦ጥሎብኝን ከሰራሽ በኃላ ስንት ኮንሰርቶች ላይ ተሳትፈሻል? ከኢትዮጲያ ውጪ የሰራሻቸው ኮንሰርቶች አሉሽ?

**<u>ራሄል</u>**፦ብዙ ኮንሰርቶችን ሰርቻለሁ በትክክል በቁጥር አላስታውስም። የመጀመሪያዬ ኮንሰርት "ሰዋዊ ኮንሰርት" ነበር ከነ ነፃነት መለሰ ፣ ከነ ጋሽ መሐሙድ እና ሌሎችም ብዙ አርቲስቶች የተሳተፉበት ኮንሰርት ነበር። ሌላው ትልቁ ኮንሰርቴ ከሰዋዊ ቀጥሎ ከአስቴር አወቀ ጋር የሰራሁት "ጨዋ ኮንሰርት" ነው። እንደነገርኩሽ በጣምብዙ ኮንሰርቶችን ሰርቻለሁ ልቤ ላይ ያሉና የማልረሳቸው ትልልቅ ኮንሰርቶቼ ሰዋዊ እና ጨዋ ኮንሰርት ናቸው። ከሀገር ውጪ ደሞ..... እነሱም ብዙ ናቸው አረብ ሀገራት ሙሉ ለሙሉ ሁሉም ጋር ሰርቻለሁ ፤ ሙሉ አውሮፖን ቱር አድርጌ ኮንሰርት ሰርቻለሁ ፤ እስራኤልም ሰርቻለሁ። አይበቃም? (ትንሽ ሳቅ)

**<u>ቅንደቤ</u>**፦ከዛው ሳንወጣ እስቲ ለኮንሰርት ከሀገር በወጣሽበት አጋጣሚ የገጠሙሽ ገጠመኞች ካሉ እስቲ አጋሪን

**<u>ራሄል</u>**፦ያጋጠመኝ ነገር የሚገርምሽ እኔ ሀገር ውስጥም ከሀገር ወጪም አጋጠመኝ ብዬ የምናገረው የለኝም። ያው ከሀገርሽ ስትወጪ ብዙ ነገሮች ሊያጋጥሙሽ ይችላሉ እኔ ግን እንዲ ብዬ የምነግርሽ ገጠመኝ የለኝም።

**<u>ቅንደቤ</u>**፦ኮሮና ቫይረስ በአለም ላይ መሰራጨቱና ስጋት መሆኑ እንደ ግል የጎዳሽ ነገር አለ?

**<u>ራሄል</u>**፦ያው እንደማንኛውም ሰው በተለይ እንደ አንድ ኢትዮጲያዊ ያለነው ገና ለማደግ በምትፍጨረጨር ሀገር እንደመሆኑ ይጎዳል።ብዙ የሚቆሙ ሁናቴዎች አሉ። አንድ አንድ ስራዎችም ቆመዋል። ግን ምንድነው ይሄ እኛ ላይ ብቻ የመጣ አይደለም አለም ላይ የመጣ ነገር ስለሆነ በብዙ መልኩ ትቀበይዋለሽ። እንደግሌ ግን የተጎዳሁትም በዚ ከቀጠለ የሚጎዳኝም ብዙ ነገር አለ። ብዙ ኮንሰርቶቼ ተሰርዘውብኛል ሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ይሁንና የኔ ጉዳት ጉዳት ተብሎ ከሀገር የሚነፃፀርም አይደለም። ብቻ እግዚአብሔር ከሱ መቅሰፍት ይሰውረን።

**<u>ቅንደቤ</u>**፦ አሜን አለምን ሁሉ ይሰውርልን ! እስቲ አሁን ደግሞ መለስ ብለን ወደግል ህይወትሽ እንግባና ራሄል የት ተወለደች የትስ አደገች? መዝፈን የት እና እንዴት ጀመረች?

**<u>ራሄል</u>**፦ ራሄል አዲስ አበባ ነው ተወልዳ ያደገችው። (ትንሽ ሳቅ) ፍል ውሃ አከባቢ በተለምዶ ፊንፍኔ ይባላል እዛ ሰፈር ነው ያደኩት። ሙዚቃ የጀመርኩት ልጅ ሆኜ ተማሪ እያለሁ ትምህርት ቤት ውስጥ ሚኒ-ሚድያ ውስጥ ነው ከዛ ከፍ እያለ ህፃናትና ወጣቶች ትያትር ቤት ገባሁ። ከዛም ቀጥዬ የተመሰገን ልጆች የመጀመሪያው ግሩፕ ውስጥ ተቀላቀልኩ። እያለ እያለ 'የኛ' ፕሮጀክት መጣ.... አሁንም እያለ እያለ "ጥሎብኝ" መጣ እልሻለሁ። (ትንሽ ሳቅ)

**<u>ቅንደቤ</u>**፦ወደ ሙዚቃው ያስገባሽ የመጀመሪያው አጋጣሚሽ ምን ነበር?

**ራሄል**፦ ያው እንደነገርኩሽ እኔ በአጋጣሚ አይደለም ሙዚቃ ውስጥ የገባሁት ያደኩበት ነው። በአጋጣሚ ሳይሆን አብሮኝ ያደገ ነው። ልጅ ሆኜ ነበር የጀመርኩት ህፃናንና ወጣቶች ትያትር ቤት ስሰራ በ 11 ዓመቴ ነበር መድረክ ላይ እዘፍን የነበረው። እና አብሮኝ ነው ያደገው ብልሽ ይቀለኛል።

**ቅንድቤ**፦ ራሄል ሴት ልጅ አለችሽ እናትነትን እና ሙዚቀኛ መሆንን እንዴት ታይዋለሽ? አልከበደሽም?

**ራሄል**፦ እውነት ለመናገር አልከበደኝም። በመሰረቱ ግን እናትነት ብቻውን ብዙ የሚከብዱ ነገሮች አሉት። ግን ልጆች ሲወለዱ የራሳቸውን እጣ ፈንታ ይዘው ነው የሚወለዱት፣ እግዚአብሔር ከምንችለው በላይ አይሰጠንም፤ እናትነትን እንደምንችለው አውቆ ነው እናት የሚያደርገን ። ስለዚህ ከምንችለው በላይ ስለማይሰጠን ሁላችንም የምንችለውን የተሰጠንን ተቀብለን ነው የምንኖረው። እና ምን ልልሽ ፈልጌ ነው እናትነት በጣም ልዩ በቃ አለም ላይ ካሉ ነገሮች ሁሉ የተለየ ስጦታ ነው፤ ምክንያቱም በዚህ አለም ስትኖሪ ሁሌ ያንቺ እንደሆኑ እርግጠኛ የምትሆኚባቸው ልጆችሽ ናቸው። ልዩ ፀጋ ነው የሚታየኝ፤ ምንም የሚከብድ ነገር አይታየኝም እንደውም ልጄን ከወለድኳት በኋላ ነው ብዙ መልካም ነገሮች የተከሰቱልኝ ማለት እችላለሁ።

**ቅንድቤ**፦ ትርፍ ጊዜሽን ምን በማድረግ ነው የምታሳልፊው?

**ራሄል**፦ ፊልም ማየት በጣም እወዳለሁ። ያየሁትን ፊልም ደጋግሜ ላየው ሁላ እችላለሁ። ሙዚቃ በጣም እሰማለሁ በትርፍ ሰዓቴ ሁለቱን ነው የማደርገው። ሙዚቃ መስማትና ፊልም ማየት።

**ቅንድቤ**፦ ከሀገር ውስጥ በትወና የማን አድናቂ ነሽ? አንድ ወንድ አንድ ሴት ብቻ ስማቸውን ንገሪን እስቲ

**ራሄል**፦ አንድ አንድ ብቻ? ኧረ ብዙ ናቸው አታስመርጪኝ,,,,,,,ግድ ከሆነ እሺ ከሴቶች የአርቲስት እድልወርቅ ጣሰው አድናቂ ነኝ። በትንሽ ሰራዎቿ ድንቅ ብቃቷን ያሳየች ልዩ አቅም ያላት አክትረስ ናት። ከወንዶች ደግሞ የግሩም ኤርምያስ አድናቂ ነኝ።




**ቅንድቤ**፦አርያዬ ነው የምትይው ሰውማን ነው/ማን ናት?

**ራሄል** ፦ከሀገር ውስጥ አርያዬ ናት ብዬ የማስባት አርቲስት አስቴር አወቀን ነው። አስቴር አወቀ ለኔ ትምህርት ቤት ነች፤ የሀገር ትምህርት ቤት ናት ብልም ማጋነን አይሆንም። ለኔ ሮል ሞዴሌ ናት አስቴር አወቀ።

**ቅንድቤ**፦እንደው ራሄል ሙዚቀኛ ባትሆን ኖሮ ምን ትሰራ ነበር?

**ራሄል** ፦ አይገርምሽም ሙዚቀኛ ባልሆን ምንም አልሆንም ነበር ። (ትንሽ ሳቅ) የእውነት ራሄል ሙዚቀኛ ባትሆን ኖሮ ምንም አትሆንም ነበር።

**ቅንድቤ**፦በህይወትሽ አድርጌው በነበረ ብለሽ የምትቆጭበት ነገር አለ? ምንድ ነው?

**ራሄል** ፦(ትንሽ ዝምታ) አይ የለም። እውነት ለመናገር እኔ የምቆጭ ሰው አይደለሁም። ሁልጊዜ በነገሮች ከህይወት አይደል የምንማረው? ሁልጊዜም የምቆጭ ሰው አይደለሁም በነገሮች ግን እማራለሁ። ወደኋላም የምቆጭ አይደለሁም ወደፊት ግን የምማር ሰው ነኝ። እና የሚቆጨኝ ነገር የለም።

**ቅንድቤ**፦ራሄልን የቅርብ ጓደኞቿ በጣም የሚያውቁት ባህሪዋ ወይንም ልምዷ ምንድነው?

**ራሄል**፡- በፊት በፊት በአርፋጅነቴ በጣም እታወቅ ነበር አሁን ግን በሚያረፍድ እራሱ እናደዳለሁ። ሌላ በጣም የምታወቀው በተጫዋችነቴ ይሆናል። የትም ልሂድ ከሰዎች ጋር እጫወታለሁ ጭንቀት አልወድም።

**ቅንድቤ**፡- "ጥሎብንን ከለቀቀች በኋላ ራሄል እራሷን ክባለች" ለሚሉት ሰዎች መልስሽ ምንድነው?


**ራሄል**፡- (ረጅም ሳቅ)…. እኔንጃ ብቻ አለ አይደል ከዝነኝነቱ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ነገሮች አሉ መሰለኝ እኔም አሁን ነው አርፍጄ የተረዳሁት። የእውነት ማንነትሽን ማወቅና መናገር የሚችለው የሚያውቅሽ ሰው ነው፤ ሁሉም ሰው ደግሞ ሊያውቅሽ አይችልም። እና እንዳልኩሽ ዝነኛ ከመሆን ጋር ተያይዘው የሚመጡ ነገሮች አሉ እና የሚመስሉን ነገሮች አለ አይደል በግምት 'ከሩቁ እንትና እንዲ ናት' ብለን እንደምናወራው አይነት ነገር….. እውነታው ግን ሰውን ቀርቦ ሳያዩ መናግር ልክ አለመሆኑ ነው። እኔ በተፈጥሮዬ እንደውም ከክባድ ይልቅ በየቦታው ነፃ ሆኜ ስጫወት ነው የምታወቀው ። እንደውም አንዳንዴ 'ኧረ ባክሽ አሁን ታዋቂ ነሽ ተጠንቀቂ' ነው የምባለው። ሰው ግን የመሰለውን የገመተውን ማሰብ ይችላል፤ 'መቼስ ለምን አሰብክ' ማለት አይቻልም።

**ራሄል**፡- በመጀመሪያ ሴትም ተሆነ ወንድ ለሁሉም ነገር መሰረቱ ፍላጎት ነው። ፍላጎት ሲኖርሽ ትገፊበታለሽ፣ ተስፋ አትቆርጪም። ከዛ ቀጥሎ ጥረት ነው፤ ለምትፈልጊው ነገር መታገልና መጣር ያስፈልጋል። ሌላው እውነተኛነት ነው፣ ለኔ ምን ግዜም የሚያሻግረን እውነት ነው። እውነተኛነታችን ያሻግረናል ፣ እውነተኛነታችን ጥግ ድረስ ያደርሰናል። በእውነት መንገድ የእውነት ጥረት እያደረግን ፍላጎት ኖሮን ከገፋንበት ያለምንም አቋራጭ መንገድ የፈለግንበት ቦታ መድረስ እንችላለን። ባለን ተሰጥኦ፣ በተሰጠን መክሊት ተጠቅመን ስኬታማ መሆን እንችላለን። ስለዚህ ሴትነታችሁ በፍፁም ወደኋላ ሊጎትታችሁ አይገባም ማለት እፈልጋለሁ።

**ቅንድቤ**፡- ኢትዮጲያዊነትን እንዴት ትገልጭዋለሽ?

**ራሄል** ፡-ኢትዮጲያዊነት ለኔ ክብር ነው። ሁሌ ነው የምለው ኢትዮጲያዊነቴ ለኔ ህይወቴ ነው፤ ማንነቴ ነው፤ ክብሬ ነው።

**ቅንድቤ**፡- ራሄል ባለፉት ሳምንታት ስለቀቅሽው አዲስ ነጠላ ዜማ "ያገሬ ሰው" እናውራ… ሀሳቡ እንዴ መጣ? ህዝቡስ እንዴት ነበር አቀባበሉ?




**ቅንድቤ**፡- የህይወት መርህሽ ምንድነው?

**ራሄል**፡- ብዙ የህይወት መርሆች አሉኝ አንዱና ለኔ ትልቅ ሀሳብ ያለው ግን "ሰበብ ወይንም ምክንያት ውጤታማ አያደርግም" የሚለው ነው። ይሄን የተማርኩት ከአንድ አካል ጉዳተኛ ስፖርተኛ ነው። ስሙን ባላስታውስም አካል ጉዳተኛ መሆኑ ስፖርተኛ ከመሆንና ስኬታማ ከመሆን አላገደውም ነበር። እና ሰበብና ምክንያት እየሰጠን እራሳችንን እናድክም፣ እሱ ውጤታማ አያደርጉምና።

**ቅንድቤ**፡- ሴት ሆኖ አንቺ የደረስሽበት መድረስ በጣም ከባድ ነው። በተለይ በኛ ሀገር በዚህ አጋጣሚ እድሉን ሳያገኙ ቤት ለተቀመጡ ሴቶች የምትያቸው ነገር ካለ።

**ራሄል**፡- "የሀገሬ ሰው"ን ለመስራት እንዴት ሀሳቡ መጣ መሰለሽ…. ያው አሁን ያለንበት በሀገራችን ላይ በመላ አለም ላይ የመጣብን መቅሰፍት አለ፤ መጀመሪያ እግዚአብሔር እሱን ይመልስልንና ይማረን ። በዚህ ጉዳይ እየወጡ ያሉ ብዙ ማስተማሪያ የሚሆኑ ስራዎች ተሰርተዋል። ብዙ ሙዚቃዎችም እየተለቀቁ ይገኛል። እና ምንድነው ውስጤ የጫረው ነገር እንዳልኩሽ በሽታው እኛ ላይ ብቻ አይደለም አለም ላይ ነው የመጣው፣ ግን መቋቋም የሚችሉ ሀገሮች በተሻለ መጠን እንደምንም እየተቋቋሙት ነው። እኔ ግን ሁልጊዜ ውስጤ የሚመላለሰው ከዚህ በሽታ ጋር ተያይዞ እዚህ በኛ ሀገር ላይ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉት በትንንሽ ነገር የሚኖሩት ያሳዝኑኛል፣ ያሰጋኛልም።



እውነት ለመናገር ከመቼውም ጊዜ በላይ እርስ በርስ መረዳዳት ያለብን ጊዜ አሁን ነው። እኔም እታች ያሉትን ሰዎች በማማከር ውስጤ የተሰማኝን እውነተኛ ስሜቴን ነው የሰራሁት ። ትንሽም ብትሆን ተስፋ መጫር ነበር ፍላጎቴ፤ አይዞን የሚል የማበረታታት መልዕክት ያለው ነው እንጂ በሽታውን ለማስታወስ አይደለም። ሀሳቤን ሳካፍላቸው ግጥሙን ናትናኤል ግርማቸው ነው የፃፈው፤ ዜማውን የሰራልኝ ምህረት አብ ይባላል፤ ቪዲዮ ላይ ስንመጣ ደሞ ተዋናይ ሄኖክ ወንድሙ ነው ዳይሬክት ያደረገው። በትብብር ነው የሰራነው ህዝቡም ካሰብነው በላይ ተቀብሎታል።

**<u>ቅንደል</u>**፡-በተጨማሪም ሰብሰብ ብላችሁ አንድ አዲስ አልበም እየሰራችሁ እንደሆነ በሶሻል ሚዲያ ይነገራል። እውነት ከሆነ ማን ማን የተሳተፈበት አልበም ነው? ሰብሰብ ብሎ ለመምጣትስ ምን አነሳሳቹ?

**<u>ራሄል</u>**፡-አዎ እውነት ነው ሰብሰብ ብለን አንድ አልበም አስመርቀናል። አልበሙ ንጋት ይሰኛል። እንደ ቀልድ የተሰራ አይደለም ያው ቫይረሱ በሀገራችን ከተከሰተ በኋላ እኛም እንደ አርቲስትነታችን በቻልነው መጠን ማበርከት ያለብን ነገር አለ ብለን ስላመንን ነው አልበሙን ለመስራት የተሰባሰብነው። አልበሙ ሙሉ ለሙሉ ተሸጦ ገቢው ቫይረሱን ለመከላከል እየተደረገ ላለው እንቅስቃሴ እንዲውል ለክቡር ከንቲባ እንጅነር ታከለ ኡማ አበርክተናል። አልበሙን ለመስራት ሀሳቡን ይዘው የተነሱት እነ ዘሪቱ ከበደ ናቸው። አልበሙም አውታር መልቲ ሚዲያ ላይ የሚለቀቅ ይሆናል። አልበሙ ላይ ቤቲ ጂ፣ ቸሊና፣ ፍቅረ አዲስ ፣ ዘሪቱ ፣ ሀይሌ ሩት ፣ ጃኒ ራጋና ሌሎችም የተሳተፉበት አሉ።

**<u>ቅንደል</u>**፡- ከራሄል ወደፊት ምን እንጠብቅ?

**<u>ራሄል</u>**፡- እንደው ፈጣሪ በምህረቱ ይሄን ግዜ ያሳልፈን እንጂ በሚቀጥለው አልበሜን እየሰራሁ ነው እሱን ይዤ የምመጣ ይመስለኛል

**<u>ቅንደል</u>**፡- እኔ ጨርሻለሁ አንቺ ቀረ የምትይው ነገር ካለ?

**<u>ራሄል</u>** ፡- በመጀመሪያ እንደ በደላችን ሳይሆን እንደቸርነቱ የማይገባኝን እየሰጠ እዚህ ያደረሰኝን ፈጣሪ አመሰግናለሁ። በመቀጠል ኤኬሌ ኤኬሌ ብዬ መጥቀስ ቢከብደኝም በእያንዳንዷ ጉዞዬ ላይ አብራችሁኝ ለነበራችሁ ወደ ፊትም ለምትኖሩትም ከልብ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ። በስተመጨረሻም ፈጣሪ ከመጣብን መዓት ይሰውረን፣ ይማረን እንደዚሁ ከቁጥር ሳያጎድል ከዚህ አስጨናቂ ግዜ የምንውጣበት ቀን ያቅርብልን።

**<u>ቅንደል</u>**፡- በድጋሚ ጊዜሽን ሰጥተሽን ከኛ ጋር ስለቆየሽ እጅግ በጣም እናመሰግናለን።

**<u>ራሄል</u>** ፡- እኔም በጣም አመሰግናለሁ። ሀሳባችሁን ጥሩ ነው በርቱ እናንተም።

****************

ቅንደል DIGITAL MAGAZINE
ምርትና አገልግሎትዎን ያስተዋውቁ!
PROMOTE YOUR SERVICE HERE!
ለበለጠ መረጃ ይደውሉ +251912178520 | +251920019699

# የቅኖች ገፅ



ዶ/ር ኣበበች ጎበና

በየትኛውም የአለም ማኅበረሰብ ውስጥ የእናትነት ቦታ በቃላቶች ከሚገለጸው በላይ ስሜታዊ ሲያደርግ መመልከት የተለመደ ከሆነ ቆይቷል። በተለይም እንደ ሀገራችን ባሉ እና በድህነት ውስጥ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ለእናትነት የሚሰጡት ትርጉም ደመቅ ብሎ ይታያል። ይህ የሆነውም አንድ እናት ልጆችዋን ለማሳደግ የምትገባበት የህይወት ፈተና እና ስንክሳሮች የገዘፉ በመሆናቸው እንደሆነ ይታመናል። ታዲያ ባሳለፍነው ሳምንት የእናቶች ቀን በደመቀ ሁኔታ በተለያዩ የማኅበራዊ ትስስር ገጾች ተከብሯል።

እንደ ሀገራችን የማኅበረሰብ የኑሮ ዘይቤ እናትነት ልጅ ወልዶ መሳም ብቻ ሳይሆን የፈተና ጅማሮ መንገድም ጭምር ነው። አብዛኛው ማለት በሚቻል መልኩ፣ የሀገራችን ማኅበረሰብ የኑሮ ሁኔታ የሚገለፀው በድህነት ነው። ለዚህም ነው እናቶች ዘጠኝ ወር በሆዳቸው ተሸክመው ብቻ ሳይሆን መከራን እላያቸው ላይ ጭነው ፣ በባሎች ግልምጫ እና ድብደባ፣ ውበታቸውን ለልጆች ሰጥተው፣ እነሱ ገርጥተው፣ ከነሱ ዛሬ ይልቅ ለልጆቻቸው ነገ መሥዋዕት የሚሆኑት። በእርግጥ አንዳንድ እናትም አባትም ሆነው ለቤተሰባቸው ፍቅር እና ለውጥ የሚጥሩ ባሎች አሉ ፤ ነገር ግን በሀገራችን ብሎም በአፍሪካ ሚስቱን ሚደበድብ ወንድ ብዙ ነው። ነገር ግን ዛሬ ስለ ባል እና ሚስት የቤት ውስጥ ህይወት ልንመክር ሳይሆን ዘመናቸውን ለልጆቻቸው ለሰጡ እና የእድሜ ልክ ፍቅርን ለኛ ህይወት ለውጥ ለተጉ ኢትዮጲያዊ እናቶች ምስጋና ልናቀርብ ወደድን።

ታዲያ በዛሬው የቅኖች ገጽ ላይ በሀገራችን ኢትዮጲያ የብዙ ወላጅ አልባ ህጻናት እናት ሆነው ለዘመናት የዘለቁት እና በብዙዎች ዘንድ 'አፍሪካዊቷ ማዘር ትሬዛ' እየተባሉ የሚወሱትን ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና በቅንነት ተግባራቸው የቅኖች ምሳሌ ስንል እናወድሳለን።
ኢትዮጲያዊቷ የደግነት ልእልት ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና 'መልካም የእናቶች ቀን ከእረጅም እድሜ ጋር' ተመኘሁልዎት። ከደግነት የበለጠ ጀግንነት የለም ጀግና ሆነው አሳይተውናል… ለእንህ እናት በየከተማው ሀውልት ቢቆምላቸው በህይወት እያሉ ብናከብራቸው ብዬ እመኛለሁ… ደግነት ሰው ቢሆን እሳቸውን ይመስል ነበር !!

# የቅኖች ገፅ



ኣብርሀም ወልዴ

## መልካም አሳቢው የኪነ-ጥበብ ሰው - ባለ ሀገሩ !!

የተለያዩ የሙያ ባለቤቶች ከሞያቸው ባሻገር ለሀገራችው የሚሆን በርካታ የመልካም ተግባራት ስራዎች ላይ ተሳታፊ በመሆን የህዝብ ልጅነታቸውን በተለያዩ ግዜያት ሲያስመስክሩ ይታያል። ነገር ግን እነዚህ ግለሰቦች በጣም ጥቂት በመሆናቸው እና መልካም ስራቸው ስላልተነገረ ተደብቀው እና ለሌሎች ምሳሌ ሳይሆኑ ይቀራሉ። ታዲያ እኛም በዛሬው የቅንድል መጽሄት የቅኖች ገጽ የቅን ምሳሌ ስንል ልናመሰግነው የወደድነው የኪነ ጥበብ ሰው ብዙዎቻችን በጉጉት ቅዳሜን እንድንጠብቅ ካደረጉን የሙዚቃ ባለሙያዎች አንዱ የሆነው እና በተለያዩ የሬድዮ  ፕሮግራሞች ፣ ተውኔቶች እና የሙዚቃ ድርሰቶቹ የምናቀው ብሎም በቅርብ አመታት የብዙዎችን ቀለብ የሳበውን የባላገሩ አይዶል በማዘጋጀት እና ተወዳጅ ድምጻውያንን በማፍራት የምናውቀው አብርሀም ወልዴ  ነው። አብርሀም ወልዴን የዛሬው የቅኖች ምሳሌ ስናደርግ ከኪነ- ጥበብ ስራዎቹ በተለይም ባለ ሀገሩ በሚል የሙዚቃ ስራዎች የሀገራችንን ታሪክ ከማስተዋወቁ እና ወጣት ድምጻውያንን በማፍራት ካበረከተው የሙያው ግዴታ በተጨማሪ በቅርቡ በ ኮቪድ 19 ምክንያት ቤተ እምነቶች ተዘግተው እማኞች ቤታቸው በሚያከብሩበት ወቅት በግል የቴሌቪዥን ጣቢያው፣ በባላገሩ ቲቪ አማካኝነት የኦርቶዶክስ እምነት የሕማማት ስግደት ፕሮግራምን በቀጥታ በማስተላፍ፣ የእስልምና ዕምነት የታህጁድ ሰላትን ከመስጅድ በቀጥታ ለሙስሊሙ ማህበረሰብ በማድረስ ለሚሰራው የመልካምነት ስራ ልናመሰግን እና የቅንድል መጽሔት የቅኖች ገጽ ምሳሌ ለማድረግ በቅተናል።

በርካታ ተቋማት የተለያዩ ድጋፎችን እና የቅንንነት ስራን እንደሚሰሩ እሙን ነው እኛም ከበርካቶች መካከል በየጊዜው ወደ ቅንነት ተምሳሌት ማጀት እያመጣን ስለምሳሌነታቸው የምናመሰግን ይሆናል እስከዛው ቅኖችን ያብዛልን እንላለን።

ነዋል አቡበከር
በ መቀሌ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት እና የኮሚኒኬሽን መምህር
newal.abubeker13@gmail.com




# ሁሰት እውነት አሰን

በተገባደደው ሳምንት የተከበረው የአፍሪካ ቀን ምንም እንኳ አለም ባለችበት ችግር ምክንያት እንደወትሮው መከበር ባይችልም እለቱ ግን አፍሪካዊ ጉዳዮች ተዘክረውበት ውሏል። አፍሪካ እንደ አህጉር ለበርካታ ሺህ አመታት አንድም በስልጣኔ ጫፍ ሌላ ግዜም በኋላቀርነት ሰንጠረዥ ቀዳሚ ተጠቃሽ ሆና የምትነሳ አህጉር የመሆኗ እውነት እጣፈንታዋ ነው።

ታዲያ በዛሬው የአጃኢብ አምዳችን አስገራሚ ስለሆነው የአፍሪካ ሀቆች ትንሽ እናነሳለን ። በርግጥ ግርምት የሚፈጥሩ ነገሮች ሁሉ ከመልካም ነገር የሚቀዱ ባይሆኑም ከግራውም ከቀኙም ከተፈጥሮውም ከሰው ሰራሹም ከታሪኩም ከፖለቲካውም በትንሹ አብረን እንገረም።

አፍሪካ በግሪኮች ስነ ቃል 'ሞቃት' ማለት ነው። ምን አልባት የአፍሪካ ስያሜ ከዚሁ ቃል መመንጨቱ እውነት ከሆነ በአለም ላይ ትልቁ በረሀ በምድሯ መገኘቱ ስያሜውን ተገቢ ሊያደርገው ይችላል ። የ54 ሀገራትና የ1.1 ቢልየን ህዝቦች መኖሪያዋ ይህች ምድር የጥንት ታሪኳ የአብዛኛው ገፅ መዳሰሻ ናቸው።

ታዲያ በዚህ ረጅም ጉዞ አፍሪካ እጅግ አስገራሚ የተፈጥሮ የታሪክ እና የአኗኗር እውነት ያላት አህጉር መሆኗ አልቀረም። በስልጣኔ ደረጃ ኢትዮጵያን ጨምሮ ማሊና ግብፅ እንዲሁም ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የሚጠቀሱ ናቸው። በአለም የመጀመሪያው ባለ ፕላን ከተማ የጥንታዊት ግብፅ 'ካሁን' ከተማ ናት ። ፅሀፍት ስለ አፍሪካ በመደነቅ ከሚተርኳቸው ትርክቶች መሀከል የኢትዮጵያ የግዜ አቆጣጠር አንዱ ነው። ይሄ ደግሞ የግል የሆነን የግዜ ቀመር ያመለክታል።

አሁን አሁን በትምህርት ተቋማት ጥራትና ብዛት ደካማ የምትባለው አፍሪካ የመጀመሪያዎቹን ዩንቨርስቲ ካቆሙ አህጉራት ቀዳሚዋ ናት። በጥንት የማሊ ስልጣኔ በእውቀት ልህቀት እጅግ የመጠቁ ሰዎች ይኖሩባት በነበረችው ከተማ በ982 የተገነባው የቲምቡክቱ ዩንቨርስቲ የ12ኛው ክ/ዘ የአፍሪካ ስልጣኔ መገለጫ ነው ።

ከእውቀት ወደ ፖለቲካው እንሸጋገር።ምንም እንኳ በአፍሪካ የፖለቲካ አለም ሀገራት መንበራቸው በሌሎች ህዝቦች እስከመመለክ የደረሱ አጃኢበተኛ መሪዎችን ከማስተናገድ ቦዝነው አያውቁም።

ለምሳሌ የኡጋንዳው ኤዲያሚን ተቀጥላ ስማቸው ሳይቀር አስገራሚ ነው። እኚህ ሰው ከስማቸው በፊት ያሉት ተቀጥላዎች እንደ ስልጣን የረዘሙ ነበሩ።ሙሉ ስማቸውን ለመጥራት እንቀፅ እንደመፃፍ ያለ ልፋት የሚጠይቅ ነው። ለዚያውም "የምድር አራዊት የባህር አሳዎች ጌታ የዘላለም መሪ " የሚሉ ተቀጥላዎች።

በአንድ ግዜ የሁለት ሀገራት ቀዳማዊት እመቤትንም አስተናግዳለች አፍሪካ ። ግሬሳ ሚሼል ይባላሉ።እኚህ ሴት በተመሳሳይ ግዜ ሞዛምቢክ እና የደቡብ አፍሪካ ቀዳማዊት እመቤት ነበሩ ።

አለም በታሪኳ እስካሁን ካስተናገደቻቸው ባለፀጋ ሰዎች እንደ ማንሳ ሙሳ ያለ ባለ ፀጋ ታይቶ አይታወቅም ። ማንሳ ሙሳ የማሊ ንጉስና የንግድ ሰው ነበሩ። ታዲያ ይህ ሰው 1937 በሞት ሲሰናበት ከ300- 400 ቢልዮን ዶላር የተጣራ ሀብት ነበረው።


ምን አልባት ለአብዛኛዎቻችን እኚህ ደግና አስገራሚ ነገሮችን መስማት አፍሪካ የተለየችና ያልተነገረላት አህጉር መሆኗን እንድናስብ ሊያደርገን ይችላል ። ምናልባትም ይሄ እውነት ሊሆን ይችላል ። አዎ በአፍሪካ ምድር ሮዝ ሀይቅ ተንጣሎ ይገኛል። ረጅሙ ወንዝም ምንጩ እዚሁ ነው። ነገር ግን ከዚህ በላይ የሚያስደነግጡ እና አንገት የሚያስደፉ እውነቶች ባለቤትም ናት አፍሪካ።

አፍሪካ የ1.1 ቢልየን ህዝቦች እናት ብትሆንም 40% የሚሆነው ህዝብ ቀለም የማያውቅ ፡ በሚልየኖች የሚቆጠር ነፍስ የሚረግፍባቸው ጦርነቶች ምድር ናት። በቆዳ ስፋት የሚስተካከላት ትንሽ ነው። ሆኖም 90% የሚሆነው አፈር አፍርቶ የሚያበላ አይደለም። በምድሯ ቢልየን ኪዩቢክ ሌትር ውሀ ገነት ከሚመስሉት ምንጮች ይንፎለፎላል። ግን 300 ሚልየን ህዝቦች የመጠጥ ውሀ ናፋቂ ናቸው። ሚልየኖች ህይወታቸው የሚረግፈው እዚህ ግባ በማይባል በሽታ ነው።


ምንም እንኳ ከአለማችን የመአድን ሀብት 30% አፍሪካ ውስጥ ሲገኝ አለም ላይ ካለው ወርቅ ግማሹ ከአንዲት የአፍሪካ ሀገር ሆድ የተገኘ ሆኖ ሳለ ፡ በቀን ብቻ 2.2 ሚልየን በርሜል ነዳጅ ከዚህቹ ምድር በየቀኑ ቢታለብምና የብረት ምርት ትልቁ መነሻ ይህችው የጥቁር ምድር ብትሆንም ህዝቦቹ ዛሬም በበሬ ከማረስ አልተላቀቁም። በልቶ ማደር ወጥቶ መግባት ለሁሉም የታደለ ነገር አይደለም።

እንዲህ ባሉ ሁለት የተለያዩ እውነቶች የተጨነቀችው አፍሪካ ታዲያ የአፍሪካ ቀን ተብሎ ሲከበር እንደወትሮው በስብሰባና በንግግር ሳይሆን በመነጠልና በማብሰልሰል ቢሆን መልካም ነው።

እንዲህ ተፈጥሮ ባልበደላት የጥቁር ምድር መጥገብ ሲቻል መራብ ፡ ሀይማኖተኛ ሳለች የሽብር እናት ፡ በረዘመ ታሪክና ባህል መሀል ልመናና ኩረጃ እጣፈንታዋ መሆኑ እጃኢኢኢኢብ እያስባለን እንደው ለምን ይሆን? በጥልቅ የምናስብበት ቀን ቢሆን መልካም ይሆናል። የለውጥ መጀመሪያ እራስን ጠንቅቆ ማወቅም አይደል?



# መዘናጋት ዋጋ ያስከፍላል !







## ውድ የቅንድል ቤተሰቦች እነዚህን ጠቃሚ መልእክቶች በቀን ተቀን ውሏችን እንተግብር

◎ እጃችሁን በሳሙና እና በውሃ በደንብ ይታጠቡ
◎አትጨባበጡ/አትሳሳሙ
◎ማህበራዊ መስተጋብርን በጣም ይቀንሱ!
◎አስገዳጅ ካልሆነ በቀር ከቤት አይውጡ!
◎አካላዊ ርቀቶትን በእጅጉ ይጠብቁ

**Yaa Lammii koo!!!**
Akkuma beekamu, yeroo ammaa kana addunyaa guutuu yaaddessaa kan jiru, Vaayiraasiin Koronaa( Covid-19), biyya keenyaafis yaaddoo guddaa ta'aa jira, kanaafuu,nutis gorsa ogeessonnii fi abbootiin amantaa , akkasumas qaamni dhimmi kun ilaallatu hundi nuuf kennanu irratti hundaawuun:-

1.Fageenya keenyaa haa eeggannu!
2.Harka keenya sirriitti bishaaniifi Saamunaadhaan haa dhiqannu
3.Amma danda'ametti Maaskii haa fayyadamnu
4. Yoo humnaa ol ta'e malee manaa bawuu dhiisuu..fi kkf..raawwachuun, ofis ta'ee lammii keenya haa eegnu!!!

◎Don't step out of home unless absolutely necessary.
◎Wash hands after everything and anything.
◎Food supply will be scarce, use it wisely
◎Allow only one member of family to step out for food, if you've any cases close to where u live, use gloves and masks
◎Go to hospitals if you have fever with a dry cough and you feel weaker than usual
◎Get enough sleep and exercise, it boosts immunity

**ሸለልትነት ዋጋ ፀኒሑ ከየክፍለና!**
◎ሰላምታና ብርሑቅ ይኹን !
◎ዝተኸበርኩም ናይ ቅንድል ኣባላት ሰድራ እዞም ጠቀምቲ መልእኽቲ ኣብ ዕለታዊ ምንቅስቃስ ነተግብሮም።!
◎ኣእዳዎም ብሳምናን መይን ይትሓፀቡ
◎ኣይትጨባበጡ /ኣይትሰዓዓሙ
◎ማሕበራዊ ርክቦም ይቀንሱ!
◎ኣድላዪ ተዘይኾይኑ ካብ ገዛ ኣይውፅኡ!
◎ኣካላዊ ርሕቀቶም ኩሉ ግዘ ይሓልው!




"ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" የሚለው የህብረተሰብ ጤና ምክር እና ተጓዳኝ የጤና አጠባበቅ እንቅስቃሴ ይፋዊ በሆነ መልኩ በሃገራችን የተጀመረበት ቀን ጥቅምት 25/1898 ሲሆን ማንኛውም ህዝብ የሽንት ቤት ጉድጓድ እየቆፈረ እንዲጠቀም በዚህ እለት አዋጅ ወጥቶ ይፋ ሆኗል። ይህ አዋጅ "ሳትቆፍር አዳሪ ተጠቅመህ ክፉ በሽታ የያዘህ እንደሆነ ቅጣት ይጠብቅሀል። መቀጫውንም ለጤና ተቆጣጣሪ ደሞዝ አደርገዋለሁ!" የሚል ነበር።

# ሰውነታችን ያቀፋቸው አስገራሚ ሀቆች


✔ አንድ ሰው በአማካኝ በአመት ውስጥ 6,205,000(ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ) ጊዜ አይኑን ገጥሞ ይከፍታል።

✔ስንኮሳተር በአማካይ አርባ ሶስት የሚደርሱ ጡንቻዎችን ስንጠቀም፡ በፈገግታ ወቅት ደግሞ በአማካይ አስራ ሰባት ጡንቻዎችን እንጠቀማለን።

✔ አንድ አማካይ ሰው በህይወት ዘመኑ አስር ሺህ ጋሎን ያክል ምራቅ ያመነጫል።

✔ሰዎች እያንዳንዳችን የየራሳችን የሆነ የተለያየ የምላስ አሻራ አለን።

✔አንድ አማካይ ሰው በህይወት ዘመኑ ልቡ 300,000,000(ሶስት ቢሊየን ጊዜ ይመታል)



✔አንድ አማካይ ሰው በህይወት ዘመኑ 48 ሚሊየን ጋሎን የሚደርስ ደም በሰውነት ውስጥ ይረጫል።

✔ለአንድ ደቂቃ ያህል ያለማቋረጥ ስንሳሳም 26ኪሎ ካሎሪ ኢነርጂ እናቃጥላለን።

✔ አንድ አማካይ ሰው ሰውነት ውስጥ የሚገኘው:-

❖የሰልፈር መጠን በአንድ ውሻ ላይ ሊኖር የሚችል ማናቸውንም አይነት ተባዮችን የማጥፋት :

❖የካርቦን ጥርቅም ዘጠኝ መቶ የሚደርሱ እርሳሶችን የመስራት፡

❖የፖታሲየም መጠን ከፍተኛ የሆነ ዕሳት የመፍጠር፡

❖የስብ ክምችት ሰባት ያህል ሳሙናዎችን የመስራት:

❖የፎስፈረስ መጠን ደግሞ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ የሚደርሱ የክብሪት ፍሬዎችን የመስራት አቅም አለው።

# ቅንድል ስንል
# በምክንያት ነው!

ቅንድል ስንል በምክንያት ነው!

የመጽሔቱ ስያሜ ‹‹ቅን - ድል›› ከሚሉ እራሳቸውን ችለው ትርጉም ከሚሰጡ ሁለት የተለያዩ ቃላት የተጣመረ ነው።አንዳንድ የአማርኛ መዝገበ-ቃለት ቅንነትን:- በመልካም ህሊና እየተመራ የሚኖር ፣ ተንኮል የሌለበት ፣ ትክክለኛ ፣ንፁ አመለካከት ያለው በማለት ሲተረጉሙት ፡ በተመሳሳይ የእንግሊዘኛው 'ዌብስተር ዲክሽነሪ' ቅንነትን( integrity) 'ታማኝ ለመሆን ብቃት ያላው እና ከፍተኛ የሆነ የሞራል መርህ ያላው' በማለት ይፈታዋል::
‹‹ድል›› የሚለው ቃል ማሸነፍን ፣ ስኬትን የሚያመለክት ፍቺ አለው።
በመሆኑም እነዚህን ሁለት የተለያዩ ቃላት ስናጣምር ‹‹ ቅን-ድል›› የሚል አንድ ጥምር ቃል ይመሰርታል። በዚህም መሰረት የሀገራችን ባህል የሆነውን የሌላውን ችግር የመካፈል ፣ እንግዳ ሲመጣ እግር አጥቦ ያለውን አብስሎ ማስተናገድ ፣ በፍቅር ተካፍሎ የመብላትን ፣ ካለው ማካፈልን፣ የተላበሰውን የማህበረሰባችን ቅንነት እንዲሁም ይህንን መልካምነቱን እንደ ድክመት ቆጥረው ባጠቁት ጠላቶቹ ላይ ከ ዶጋሌ እስከ አደዋ ከ መተማ እስከ ካራማራ ፣ ከ ምዕራብ እስከ ደቡብ በአንድ ላይ ተሞ ድል አድራጊነቱን ያስመሰከረበትን ጀግንነት ፣ ድል ማድረግን ወርሰን እንሆ እኛም በዘመናችን የገጠመንን የክፋት ፣ የመጠላላት፣ የስሜታዊነትን ፣ የመለያየትን እንዲሁም አላዋቂነትን በቅንነት ድል ልናደርግ ቅን-ድል ብለን ብዕራችንን ፣ ቅን-ድል ብለን ወረቀታችንን ፣ ቅን-ድል ብለን መጽሔታችንን ሰይመናል።

እንኳን ለአንደኛ አመት የምስረታ በዓላችን በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን!

ቅንነት ድል ያደርጋል!!



ፊራኦል መስፍን
በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የአዕምሮ ሀኪም እና መምህር
firaolmesfin8@gmail.com

# በኮሮና ወቅት ሊወሰዱ የሚገቡ አምስት ስነልቦናዊ እርምጃዎች

የኮሮና ወረርሽኝ ሁላችንንም ከአዳዲስ ፈተናዎች ጋር ፊት ለፊት አጋፍጦናል።የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች እጅግ አይለዋል፤ ምክንያቱም አብዛኛውን የንግድ ሥራ መሥራት ስላልተቻለ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ሥራ አጥ አድርጓል። የጤና ችግሮችም እንደዋዛ የሚታለፉ አይደለም - በኮሮና ምክንያት ብቻ ሳይሆን ፣ ወረርሽኙ የጤና እንክብካቤ ስርዓታችን እና ሀብታችንን ስለሚቀንሰው ተገቢውን ህክምና ያላገኙ ሰዎች ወደ ሞት ሊያመሩ ይችላሉ።

ይህም አልበቃ ብሎ ፣ ፈታኝ የአእምሮ ጤና ሁኔታዎች ያጋጥሙናል። በኮሮና ምክንያት ወደ ውጭ መሄድ ስለፈለግን ብቻ "ውጭ መውጣት" ከቶ አይታሰብም። ይልቁንም በተቻለ መጠን ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለመገናኘት እንገደዳለን። ወደ ገቢያ እንኳ የምናደርጋት እያንዳንዱ ጉዞ የሚሰላው በስጋት ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሳናስበው በድንገት የራሳችንን ፊት እየነካካን ስላለመሆኑም ማረጋገጥ አለብን። ስለሆነም ቤትን ለቅቆ መውጣት ማለት ዘወትር ንቁ መሆንን የሚጠይቅ ከባድ ነገር ነው ማለት ነው። እኛ እራሳችን ብቻ የቫይረሱ ሰለባ እንሆን ይሆን ብለን የምንፈራዉ ነገር ብቻ አይደለም ነገሩ ፣ የምንወዳቸው ሰዎች በበሽታው እንዳይጠቁ እና ለእኛ ቅርብ የሆነ ሰው እንዳናጣ አዕምሯችን በስጋት ይወጠራል። በእውነቱ ፣ በኮሮና ምክንያት የተለያየ ዓይነት ኪሳራ ሊያጋጥመን እንደሚችል እሙን ነው ፣ ሊደርሱብን ስለሚችሉ ኪሳራዎች ቀድመን እራሳችንን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ስለ ወደፊቱ እርግጠኛ አለመሆን ጋር ተያይዞ ያለው የማያቋርጥ ውጥረት የስነልቦና ህመም የሚስፋፋበት አውድ ይፈጥራል።

በዚህ ምክንያት ፣ አሁን ከምንጊዜውም በበለጠ ፣ ለአእምሮ ጤንነታችን ትኩረት መስጠት አለብን። ከዚህ በመቀጠል ፣ የኮሮናን ችግር በተሳካ ሁኔታ ለመቋቋም የሚያስችሉንን አምስት የስነ-ልቦና እርምጃዎችን እንመለከታለን ። እንጀምር ...

## እርምጃ #1 ከስሜቶች ጋር ይገናኙ

እንደ ፍርሃት ፣ ሀዘንና አልፎ ተርፎም በፍርሀት ባሉ ከባድ ስሜቶች ውስጥ ከተጠመድን ሕይወት ከባድ ይሆንብናል። እያንዳንዱ ትንሽ እርምጃ ከባድ ሥራ ነው፣ እናም አጠቃላይ ትኩረታችን "መጥፎ" ስሜቶችን ማቆም ላይ ያተኮረ ይሆናል ። በተመሳሳይ ሰዓት ፣ በትክክል የሚረዱንን (ልክ እንደ ትክክለኛ የአመጋገብ ስርዓት እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያሉ) ለህይወታችን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን እናቆማለን።
በዚህ ወረርሽኝ መካከል ስሜታችን ትርኢቱን እንዲያከናውን አለመፍቀድ አስፈላጊ ነው። ይህ መጥፎ ስሜቶችን ያስወግዳል ማለት አይደለም፤ ግን እራሳችንን በእነሱ ላይ እርምጃ ሳንወስድ ስሜቶችን እንዲሰማን መፍቀድ ነው። "ጥሩ" ስሜቶችን ለማስገደድ አይሞክሩ ፣ ነገር ግን በስሜቶችዎ ክፍት እና ሩህሩህ ሆነው ለመቆየት ይሞክሩ። ትንሽ፣ የተረበሸ ልጅ ሲገጥሞት እንደ ሚያደርጉት ሁሉ ያዙት። ደግ ይሁኑ። ሰውነትዎን ያዳምጡ። ከዚያ በሚቀጥሉት ደረጃዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉትን መረጃዎች የያዙ መሆን አለመሆኑን ይመልከቱ ። ለምሳሌ ፣ ፍርሃት ወይም ሀዘን ከሌሎች ጋር መገናኘትን ለመደገፍ ወይም ደህንነታቸውን ለመጠበቅ እርምጃዎችን መውሰድ ጥሩ መንገድ ሊሆን ይችላል።

## #2 ከትኩረት ጋር ይገናኙ

ባለፉት ሳምንታት እና ወራት ውስጥ ዓለም ምን ያህል እንደተቀየረ አስገራሚ ነው ። ከሁለት ወራት በፊት ፣ ሁሉም ነገር እንደ ምንግዜውም ይመስል ነበር። እናም በግዴለሽነት አፍንጫን ማከክ እና እጅን ለመጨባበጥ መዘርጋት እጅግ ቀላል ነገር ነበር ። ነገር ግን ይህ ከእንግዲህ ወዲህ አይቻልም ። ይህ ጉዳይ ምን ያህል ጊዜ እንደሚቀጥል ግልፅ አይደለም። ለወራት? ወይስ ለዓመታት?

ስለወደፊቱ እርግጠኛ በማንሆንበት ወቅት ፣ አዕምሯችን በደመነፍስ ነገሮችን ማካሄድ ይወዳል። ወደፊት ስለሚሆነው አስደንጋጭ ሁኔታዎችን በማሰብ ፣ እና ወረርሽኙ እንዴት በእኛ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በማሰብ አዕምሮአችን የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳል። ለምሳሌ፣ ብዙ ሰዎች ስለ ሱቆች መዘጋት ይጨነቃሉ ፣ በዚህም የተነሳ የተለያዩ ምግቦችን፣ የንፅህና የመጠበቂያዎችን እና የመሳሰሉትን በጅምላ ገዝተው አከማችተዋል ። ምናልባትም የዓመት ፍጆታቸውን ሸምተዋል ። በአጋጣሚ ፣ ብዙ ይህንን ያደረጉ ሰዎች አሁን የስጋታቸው አለመከሰቱን እየተገነዘቡ ነው እናም አንዳንዶች በጅምላ ገዝተው ያከማቿቸውን ነገሮች፣ "ልገሳን" ጨምሮ በተለያየ መንገድ ተመላሽ ለማድረግ እየሞከሩ ነው። ዛሬ ላይ አተኩር ። ትኩረትህን ዛሬ ላይ ማድረግህ ወሳኝ ጉዳይ ነው ።

## #3 ከሌሎች ጋር ይገናኙ

ማህበራዊ መራራቅ የሚያስደስት ነገር አይደለም። በኮሮና ምክንያት ጓደኞቻችን እና ቤተሰቦቻችን እኛ እንደቀድሞው ማየት አንችልም ፣ ይህም ትልቅ ፈታኝ ሁኔታን ይፈጥራል ። እኛ ማህበራዊ ፍጥረታት ሆነናል ፣ ቢሆንም ለደህንነታችን ሲባል የአካላዊ ንክኪ አላስፈላጊነት በደንብ ተገልጿል ። ለጊዜው ፣ ሌሎችን መንካት መተው አለብን ። ሆኖም ግን ፣ አካላዊ ግንኙነታችንን ስለገደብን ብቻ ግንኙነታችንን ማቆም አለብን ማለት አይደለም ። የኒውዚላንድ የጤና ሚኒስትር ዶክተር ዴቪድ ክላርክ በሕብረተሰቡ ንግግር ውስጥ አካላዊ ልዩነት የማያስፈልግ እንጂ ማህበራዊ መራራቅ አላስፈላጊነት ላይ ትኩረት እንዳደረጉ በአፅንኦት ገልፀዋል ። በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ እያለን አካላዊ ርቀትን መጠበቅ አለብን ።



በበይነመረብ እና በስልክ በኩል ፣ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ይህን ማድረግ እንችላለን። ሁለት ሜትር ርቀት ቢገድቦትም ጊዜ በመውሰድ፣ ለምትወዷቸው ሰዎች ይደውሉላቸው ፣ እነሱን ለመከታተል ጊዜ ይስጡ ።

## #4 ከእሴቶች ጋር ይገናኙ

የኮሮና ሁኔታ ሁላችንም ቀኖቻችን እንዲስተካከሉ አስገድዶናል። ጠዋት ሥራ ለመግባት ታክሲ ላይ መጋፋት? ከዚህ በኋላ አይቻልም። በየቀኑ ከሥራ በኋላ ከወዳጆችዎ ጋር ሰብሰብ ብሎ መዝናናት? ጥሩ ሀሳብ አይደለም ። በአጭሩ ፣ በሕይወታችን ውስጥ የነበሩ ልማዶቻችንን አስቀርቶብናል ፣ እናም በአንድ ወቅት በደስታ እና ትርጉም ሲሞሉልን የነበሩ ብዙ ልምዶቻችን በድንገት እንደ አማራጭ እንዳናስባቸው አድርጎናል ። ይህ ችግር ይፈጥራል። ብዙ ሰዎች ከእንግዲህ ለእነሱ በእውነት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ማድረግ አይችሉም። ለአንዳንዶች ዓላማቸውን ማለትም የሕይወት ደማቸውን እንደ መውሰድ ነው። በዚህ አስጨናቂ ጊዜ ውስጥ ከዓላማዎቻችን እና እሴቶቻችን ጋር፤ ከልባችን ቅርብ የሆነ ነገር ጋር መገናኘታችን በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በህይወታችን ውስጥ ዋጋ የምንሰጣቸዉን እሴቶች እንፈልግ።

## #5 ከድርጊት ጋር ይገናኙ

ብዙ ሰዎች ከመቼውም በበለጠ አሁን ነፃ ጊዜ አላቸው። ከዚህ ቀደም በሥራ ተወጥሮ በመዋል፣ ጓደኞቻቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመጎብኘት ያነሰ ጊዜ ይሰጡ ነበር። በሌላ አቅጣጫ ካየነዉ፣ ይህ ሁልጊዜ ማድረግ እየፈለግን ያልተሳኩልንን ነገሮች በመጨረሻ ለማድረግ ትልቅ መስኮት ይከፍታል። ቢሆንም ግን ፣ ብዙ ሰዎች ግቦቻቸውን ለማሳካት ይህንን ጊዜ ሲጠቀሙበት አይስተዋሉም።
ይልቁንም አብዛኛዎቹ ሰዎች በትክክል መሥራት፣ እንቅስቃሴዎችን ማለፍ እና ነገሮችን መተው ይጀምራሉ። ምክንያቱም በጥብቅ መከተል የሚያስፈልጋቸው ጥብቅ መርሃግብር የለም፤ ማንም የሥራ ባልደረባው ወይም ጓደኛ እነሱን ተጠያቂ ሊያደርጋቸው አይችልም።

#ቅንድል

**የቅንድል ዲጂታል መፅሔት የ1ኛ አመት ክብረ በዓል!**

ከሀሳባውያን ማጀት ወጥተን ወደ ተግባራውያን  ዕልፍኝ ከተሸጋገርን እነሆ አንድ አመት አስቆጠርን። የቅንድል ዲጂታል መፅሔት አንባቢያን እና ቤተሰቦች ያለ እናንተ ማበረታት እና ድጋፍ አንድም እርምጃ መራመድ አንችልም ነበር።  እናንተ ለሰጠችሁን በዋጋ ለማይተመነው የቅንነት ድጋፍ ከልብ እናመሰግናለን።
ለመጪው ትውልድ የሚጠፉበትን ቂም ፣ ዘረኝነት ፣ አለማወቅ እና እራስ ወዳድነት ከማውረስ ይልቅ የሚኖሩበትን እውቀት ፣ ፍቅር ፣ አንድነት ፣ ሀገር ፍቅር እና ምክንያታዊነት እናውርስ።
ቅን እና መልካም ሆነን ከተዋደድን በፍቅር የማይሸነፍ የለም!
ኑ የቅኖች ፣ የምክንያታዊና ሀገር ወዳድ ትውልድ እልፍኝ ወደ ሆነው ቅን-ድል  ኢትዮጲያ የወጣቶች ህብረት ይቀላቀሉ።
ቅን እናስባለን ፣ ቅን እናወራለን ፣ ቅን እንሰራለን!!!



ቅንድል ዲጂታል መፅሔት ከ TIKVAH -ETH ጋር በመተባበር ከአፍንተ ከቤተሰቦቻችን የተገኙ ለሰበታ ቤተ መፅሐፍት ቤት ግቢ የሆኑ ከ700 በላይ የትምህርት መፅሐፍት ፡ ፡



የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ያዘጋጀት ክፍል አባላት በሚኒሊክ ጎዳና አረንጓዴ አሻራ ለማኖር ቦታ ኢያዘጋጁ እና አሻራቸውን አሳርፈዋል።



ቅንድል ዲጂታል መፅሔት በመቀሌ ዩኒቨርስቲ በ2011 ተመራቂ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ያዘጋጀው "IGNITE THE MIND" ፎረም



ቅን ድል ኢትዮጲያ ቤተሰቦች በ እንደራሴ ፕሮግራም ላይ ተማሪዎችን ሲያስተናግዱ።











#ቅምሻ


ቤቲ ልክነሽ
የአመለካከት ለውጥ አሰልጣኝ እና አማካሪ፣
የመክሊታ- ሰብእ ልዩ አነቃቂ ኢቨንት አዘጋጅ
amenbetselot191gmail.com


# " የምትሻው ነገር ሊሆን ምን ያህል እንደቀረህ ስለማታውቅ እስኪዘንብልህ ጽረስ ማንቆርቆርህን ቀጥል "

ወዳጄ ነገሩ እንዲህ ነው....
ጊዜው አሜሪካ 'የወርቅ ትኩሳት' ተብሎ በሚጠራው አባዜ የተለከፈችበት፤ ሁሉም ሰው ወርቅ ለመቆፈር 'ወርቅ ይገኝበታል' ወደተባለበት ቦታ የሚጎርፍበት ነበር። በዚህ ጊዜ የንግዱ ባለሞያው የአቶ ዳርቢ አጎትም ጉዳዩን ሰምቶ ወደ አንድ ተራራ ያመራል። ብዙ ራዕይ ሰንቋል።ወርቁን አግኝቶ የሚኖረውን ሀብት እያሰበ በጉጉት እና በአዲስ ጉልበት ወደ ቦታው አመራ። በቦታውም ደረሰ፤ መቆፈር ጀመረ። ቆፈረ... ቆፈረ... ከሳምንታት በኋላ... አንዲት ብልጭ የምትል ነገር አየ። ዓይኑን ማመን አልቻለም፤ የተብለጨለጨው ነገር ወርቅ ኖሯል። በደስታ እጅጉን ፈነጠዘ። ይህንን ወርቅ ግን በትንሹ ለመውሰድ አልፈለገም። ይልቁንም በደንብ እና በስፋት አድርጎ ለመዛቅ እንጂ! ይህንን ለማድረግ ግን አካፋ እና ዶማ ብቻ በቂ አልነበረም... አዲስ እና በብዛት የሚቆፍር ማሽን አስፈለገው። ይህንን ለመግዛትም ወደ ሜሪላንድ ከተማ ተመለሰ።

በከተማው ውስጥ ለነበሩትም ባለሀብቶች ያገኘውን ነገራቸው። እነርሱም ተደሰቱ። ገንዘባቸውንም አሰባስበው እና በብዛት የሚቆፍረውን ማሽን ገዝተው ላኩት። እርሱም ደግሞ አቶ ዳርቢን ይዞ ወደ ቦታው ተመልሶ መቆፈር ጀመረ። ቆፈሩ፣ ቆፈሩ። የመጀመሪያው ቁፋሮ ሙሉ ወርቅ ሆነ። እጅግ ተደሰቱ! በዚህ አካሄድ ምን ያህል ሀብታም እንደሚሆኑ እያሰቡ በደስታ ይሳሳቁ ጀመር። የተቆፈረው ወርቅ በአጠቃላይ ወደ አንድ ትልቅ ወርቅ አቅላጭ ዘንድ ተላከ ከዚያም ደግመው ቁፋሮ ቀጠሉ።
ቢቆፈር... ቢቆፈር... ቢቆፈር... አንዲት እፍኝ ስንኳ ሊገኝ አልቻለም! በዚህ እጅግ አዘኑ። ተስፋ ቆረጡ። ከአሁን በኋላ ወርቅ አናገኝም ብለው፤ ትልቁን መቆፈሪያ ማሽንም ለአንዱ ብረት ገዢ ሸጠውለት ወደ ቀያቸው ተመለሱ። በዚህ ጊዜ ግን የመቆፈሪያ ማሽኑን የገዛው ሰውዬ፤ ወርቅ ቆፍረው አለማግኘታቸውን ሰምቶ ነበርና ወደ አንድ የማዕድን ተመራማሪ ዘንድ በመሄድ ሁኔታውን አጫወተው።

በዚህ ጊዜ የማዕድን ተመራማሪው ፈገግ እያለ "አይይ... ያሳዝናል። እነዚህ ተስፋ ቆርጠው የሄዱት ሰዎች ምንም ስለ ማዕድን ቁፋሮ የሚያውቁት ነገር የለም ማለት ነው። " ሦስት ክንድ ሲቀራቸው ተስፋ ቆርጠው ሄዱ!" ይለዋል። ይህንን የሰማው ብረት ገዢም እነ ዳርቢ ይቆፍሩበት ወደነበረው ቦታ ሄዶ እነርሱ የተዉትን መቆፈር ቀጠለ።

ቆፈረ... ቆፈረ... ቆፈረ...
በመጨረሻም በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላርን ያስገኘለትን ወርቅ እንደጉድ መዛቁን ቀጠለ!
ይኸውልህ ወዳጄ
ለምትፈልገው ነገር መቼም ተስፋ አትቁረጥ! የሞት መጀመሪያው ተስፋ መቁረጥ ነውና ስለዚህ በርታ። ለሽልማትህ ሦስት ክንድ ነው የቀረህ፣ ጀግነህ ቆፍር! ሁሌም ስኬት የሚገኘው ከድካም በኋላ ነው።
ምን አለ ትንሽ መቅረቱን ሳታውቅ ያቋረጥከው/ሽው??
ትምህርት?
የፍቅር ግንኙነቶች?
ስራ?
ምን ??????

በህይወት ጎዳና አንድ እርምጃ ወደፊት ስትራመድ ብዙ መንገድ ወደ ሁዋላ ሊመልሱህ የሚችሉ ፈተናዎች እንደሚገጥሙህ አምነህ ተቀበል። አንተ ግን ሁሌም ህልምህን ወደፊት ተመልከት። ከቻልክ ሩጥ፣ ካልቻልክ ተራመድ፣ ብቻ ወደ ኋላ የለም፤ ሁሌም ወደፊት። በጊዜው መድረስህ አይቀርም። እናስተውል ካለፈው የፊቱ ይበልጣል። ያቋረጠ መቼም አያሸንፍም!!! ለማሸነፍ መታገስ እና እስከመጨረሻው መቆፈር ግድ ነው። እራሳችንን እንፈትሽ... ስኬት ዋጋ ያስከፍላል ፍሬው ግን ጣፋጭ እና አስደሳች ነው። መልካም የተባረከና ስኬታማ ቀን ይሁንልን። የስኬት ማማ ላይ እንገናኝ።

## ★★ወርቃማ አባባሎች★★

★ "ፍቅር ለሌሎች በበጎነት የምትኖርበት ቋሚ ቃልኪዳን ነው።"

★ "ጣፋጭ ለመሆን በቂ ደስተኝነት ፣ ጠንካራ ለመሆን በቂ ሙከራ ፣ ደስታ ለማግኘት በቂ ተስፋ ፣ ሰው ለመሆን በቂ ፍቅር ይኑርህ!"

★ "ጨለምተኛ ሰው ከየትኛውም ጥሩ አጋጣሚ ውስጥ አስቸጋሪ ነገሮችን ሲመለከት፣ የብሩህ ተስፋ ባለቤት የሆነ ሰው ግን ከችግሮች ውስጥ መልካም አጋጣሚዎችን የሚመለከት ነው።"
(ዊንስተን ቸርችል)

★ "መጥፎ ስሜትን በሌላ ሰው ላይ ማንፀባረቅ ማለት በራስ ላይ ጉዳት እንደመፍጠር ይቆጠራል።"
(ቡድሀ)

★ "ፍቅር የሌለበት ህይወት ልክ ፍሬ እንደሌለው ዛፍ ነው።"
(ኢነርስቴስ)



እናናስ ግርማይ
የሥነ-ማህበረሰብ ባለሙያ
britanitam@gmail.com



# ለምን ላግባ?

ጋብቻ በማህበረሰብ ጥናት መዝገበ ቃላት ላይ እንደተቀመጠው ለዓቅመ አዳም በደረሱ አንድ ወንድና ሴት መካከል የሚደረግ ጋብቻና የራሱ የሆነ ህግና ግዴታዎች ያሉት ነው ይልና፣ ነገር ግን አሁን ዘመናዊ አስተሳሰብ ባለው ህብረተሰብ (Contemporary society) ውስጥ ደግሞ ትዳር ወይም ጋብቻ ነፃ አስተሳሰብ (Liberal) እየሆነ በመምጣቱ አብሮ መኖር (Cohbitation) እየተመረጠ መሄዱን ያስቀምጣል።

በሃገራችን የቀደመ ታሪክ ጋብቻ በሁለቱ ተጋቢዎች ፍላጎት ተመርኩዞ የሚደረግ እንዳልነበረ ይታወቃል። ለምሳሌ ሁለት የሚዋደዱ ሰዎች የበለጠ ቅርበታቸውን ለማጠናከር ልጅህን ለልጄ በማለት ልጆች ገና ሳይፀነሱ ይሰጣጡ እንደነበርና በተጨማሪም በሁለት ማኅበረሰብ ውስጥ ትስስር ለመፍጠር ወይም የተጣሉ ማኅበረሰቦችን ለማቀራረብና እርቅ እንዲፈጠር ልጆቻቸውን በማጋባት ኅብረት ያደርጉ ነበር። ኾኖም ግን በአሁኑ ጊዜ ሕፃናት 18 ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ እዳይፈፀሙ በመደረጉ ባህላዊ ጋብቻ እየቀነሰ መጥቷል። እዚህ ላይ ለመጥቀስ የፈለግሁት በሃገራችን ብዙውን ጊዜ ማኅበራዊ፤ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዳንዴም ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተጋቢዎችን ፍላጎት ሳያጤን በቤተሰብ፤ በጎረቤት በዘመድ አዝማድ ፍላጎትና ህልም ላይ ተመስርቶ ጋብቻ እንደሚፈጸም ነው።
ታድያ እንባቢያን ልብ እንድትሉ የምፈልገው በእርግጥም በእድሜ የበሰሉ ስለ አጠቃለይ ቤተሰብ፤ አካባበቢ እና የማኅበረሰብ ሁኔታ ትልቅ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ለተጋቢዎች አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ ማድረጋቸው፣ በጣም ጠቃሚና ወደፊትም መቀጠል ያለበት ነገር ቢሆንም፣ በጋብቻ ስም በሁለቱ ተጋቢዎች ህይወት ላይ ሁሉም እጁን እያስገባ ጋበቻ ወደ አልተፈለገ መጠላለፍ እንዳይገባ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ለማለት ነው። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ተጋቢዎች በጥሩ ሁኔታ አስበውበትና አቅደው ጋብቻ ስለማይፈፀሙ ከእነርሱ የሚፈጠሩት ህፃናት በሁለቱ ወላጆች እንክካቤ ባለማደጋቸው በትውልድ ላይ ትልቅ የማኅበረሰብ ቀውስ በማምጣት ላይ ይገኛል።

እዚህ ላይ ተጋቢዎቹ እራሳቸው ስለሚያገቡት ሰው በጥልቀት መርምረዉ ማወቅ አለባቸው ስል Dr. Jone Gray "Men are from Mars and Women are from Venus" በሚለው መጽሐፋቸው እንዳስቀመጡት 'ወንድና ሴት ከሁለት 'ፕላኔት' የመጡ ያህል ልዩነት እንዳላቸውና፣ ይህንኑ ልዩነት ለይተዉና አውቀዉ በአግባቡ ሊያጣጥሙት ካልሞከሩ ወደማይፈልጉት ችግር ሊከታቸዉ ይችላል' ይላሉ እኔም አባባሉን እጋራዋለሁ።

ከላይ የዘረዘርኩት እንዳለ ሆኖ ወደ ርዕሴ ስመጣ... ብዙውን ጊዜ ሰዎች ማግባት ሲፈልጉ ራሳቸውን መጠየቅ ያለባቸዉን ጥያቄም በቅደም ተከተል ባለማስቀመጣቸዉ ወደ ሌላ ቀውስ ይገባሉ። ለምሳሌ አንድ ሰው ለምን ላግባ ብሎ ራሱን ከመጠየቁ በፊት፣ ማንን ላግባ ወደ ሚለው ጥያቄ ሲዘል ወደ ትክክለኛው የጋብቻ ዓላማ እንዳይገባው ስለሚያደርገዉ ነገ ወደ ፍቺና ሌላ የትዳር ቀውስ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል።

ለምሳሌ አንድ ለማግባት የፈለገች ሴት ማንን ላግባ ብላ ራስዋን ስትጠይቅ መጀመሪያ ለማግባት የፈለገችበት ዋነኛ ምክንያት በውስጥዋ ማግኘት የምትፈልገውን በጋብቻ በኩል በአጭሩ ለማግኘት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ሀብታም መሆን ስለምትፈልግ ሀብታም ሰው ማን ነው ብላ መፈለግ ትጀምራለች ወይም እድሜዋ እየገፋ ከሆነ ደግሞ ቶሎ ልጅ ለመውለድ ማንን ባገባ ይሻላል በማለት እና ብቸኝነት ስላስቸገራት ወይም ሁሌ መዝናናት ስለምትፈልግ ይህንን ሊያሳካላት የሚችለውን ለማግባት ፍለጋዋን ትቀጥላለች። እዚህ ላይ ይህች ሴት ክቡር ከሆነዉ ጋብቻ ማግኘት የምትችለዉን ትሩፋት ለማግኘት ሳይሆን በማግባትዋ ብቻ በአቋራጭ ልታገኝ የነበረውን የተደበቀ የውስጥ ፍላጎቷን ባለማግኘትዋ እንደገና ይህንን ሊሰጣት የሚችልን ሰው ለማግኘት ፍለጋ ትቀጥላለች።

እዚህ ላይ ለምን ላግባ ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ በቂ የሆነ ምክንያት ማግኘት ሳንችል ማንን ላግባ ወደሚለው ስንሄድ ከላይ ወደ ጠቀስኩት አዙሪት መግባታችን አይቀሬ ነው። ለማግባት ከራስ የመጣ ፍላጎት ሲሆን፣ ለምን ላግባ ብለን ስንጠይቅ ብዙ ጊዜ ጥሩ መልስ ለማግኘት እንችላለን። ስለዚህ ለምን ላግባ ብለን ስንጠይቅ የምናገኛቸው ምክንያቶች ሁሉ ከስሜት ብቻ ያልመጡ፣ በቂ፣ አሳማኝና ዝርዝር ምክንያት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። ታዲያ ይህ ለምን ላግባ በሚለው ጥያቄ ዙሪያ እራሳችንን ስንመረምር መጀመርያ ሌላ ሰው ወደ ህይወታችን ከማምጣታችን በፊት ዝግጁ ስለመሆናችን መጠየቅና የሚገባንን ሁሉ ፈትሸን፣ ትክክለኛ ቁመና ላይ ስለመድረሳችን የሚያረጋግጥ ሂደትን አለብን። Dr. Myles Munroe ስለ ጋብቻ ባደረጉት ንግግር "ብዙውን ጊዜ ተጋቢዎች ሁለቱም ግማሽ ብርጭቆ ይዘው በመምጣት፣ አንዱ የአንዱን ጉድለት እንዲሞላ ጠብቆ ይገባና ሳይሞላለት ሲቀር ግጭትና ጥል ይጀመራል" ብለዋል። ይህን አባባል እኔም እጋራዋለሁ። ጋብቻ ጎዶሎ መሙያ ሳይሆን የህይወት ዓላማን ለማሳካት የአብሮነት ጉዞ ነው።

ተጋቢዎች በተናጠል የራሳቸው የሆነ ሙሉነትና ብቻቸውን ለመኖር የሚስፈልጋቸው ሁሉ እንዳላቸው ካረጋገጡ በኋላ ወደ ህይወታቸው የሚጋብዙት ሰው እንዲጨምርላቸው የሚፈልጉት እሱነቱ/ቷ ብቻ ይሆናል። እንግዲህ ለምን ማግባት እንዳለብን በትክክል ካወቅን፣ ማንን ላግባ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና ትክክለኛዉን የትዳር ጓደኛ ለማግኘት ዙሪያችንን በማስተዋል በጥልቀት በመፈተሽና በመመርመር የምናገኘዉ ይሆናል።
ይህም ሁለቱን ተጋቢዎች ጠንካራ ኅብረትና በመንፈስ የተዋሃደ ማንነት እንዲኖራቸዉ ስለሚረዳ ወደ ሚፈልጉት የህይወት ከፍታ ለመድረስ ብዙም አይቸግራቸውም። የዚህም ስኬት መሠረቱ ማንን ላግባ ሳይሆን ለምን ላግባ ለሚለው ጥያቄ ቅድሚያ በመስጠት በብስለት መርምረን ትክክለኛ መልስ በመስጠታችን ነው።



ዮናስ ጋማርቆስ
lijyoha@Gmail.com


ሰላም! ውድ የቅንድል ዲጂታል መጽሔት ቤተሰቦች እንደምን ቆያችሁ?
እንደተለመደው ዛሬም በእልፍ ገፃችን በቅርብ ከወጡ ፣ ቆየት እስካሉ መጽሀፍትን እንጠቁማችኋለን። ታድያ ጊዜው እቤት ውስጥ የምናሳልፍበት በመሆኑ ጊዜያችንን መፅሃፍቶችን በማንበብ እንድናሳልፍ አበረታታችኋለሁ።

ቤት በመሆን ራሳችንን እና ቤተሰቦቻችንን እንጠብቅ!በማንበብ እና ራስን በመጠበቅ ለትውልድ እንትረፍ!
"ማንበብ የህይወት ቁልፍ ነው!"





## ኩል እና ጥላሸት

ደራሲ: ገጣሚ በላይ በቀለ ወያ
ገፅ ብዛት: 109
ዋጋ: 71 ብር
ይዘት: ግጥም




## ጥንተ ዮን

ደራሲ : በላይነህ ታደሰ
ገፅ ብዛት: 270
ዋጋ: 151
ይዘት: ታሪክ / ፍልስፍና / ፖለቲካ




## ቀላሉን ነገር አታካብድ

አዘጋጅ: ሪቻርድ ካርሰን
ትርጉም :- ዶ/ር ዮናስ ላቀው
ገፅ ብዛት: 140
ዋጋ: 71.20
ይዘት: ስነ-ልቡና
አታሚ: ማንኩሳ




## አለመኖር

ደራሲ: ዳዊት ወንድማገኝ ( ዶ/ር )
ገፅ ብዛት: 373
ዋጋ: 150
ይዘት: ስነልቦናዊ ልቦለድ




## የምድራችን ጀግና

ጸሀፊ: ዘነበ ወላ
ገጽ ብዛት: 520
ዋጋ:200 ብር
ይዘት:የህይወት ታሪክ
አታሚ:ማንኩሳ



#ትዝብት

ቀለዮጳ ደስታ
ጅማ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፣ ደራሲ
cleopadada2012@gmail.com

# የጤና ባለሙያዎች እና ህመማቸው

“ ጀረ አትመናቸው” አለ አንደኛው ተዋናይ- ‘ሚስቴን ዳርኳት’ በተሰኘው ፊልም። “ እንቅርት ታመህ ትርፍ አንጀት የሚያወጡበት.... እዚህ ሆድ ዕቃህ ውስጥ ሹካ ቢላ ምናምን የሚረሱበት ሀገር...... ምን እመንካቸው” ብሎም ቀጠለ።
ዓለማችን ላይ አስቸጋሪ ከተባሉት ስራዎች ውስጥ ግንባር ቀደም መውሰድ ያለበት የትኛው ይመስላችኋል? ወታደርነት፣ መምህርነት፣ አካውንታንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት፣ ወይስ አክቲቪስትነት? እንዳቸውም ክብደታቸው በህክምና መነጽር ሲታይ ቀልሎ ይገኛል። ምናልባት ወታደር ስጋና አጥንቱን ከስክሶ ሀገሩን ይጠብቃል፤ መምህር የህክምና ባለሙያውን ያስተምራል፤ አካውንታንት ለህክምና ባለሙያው ደመወዝ ይከፍላል፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መመሪያን ያወጣል... ህክምና ግን ከዚህም በላይ ነው።

እስቲ ወደሆስፒታል ጎራ በሉ። ድንገተኛ ክፍል ግቡ... አለማችን ላይ ከሚያሰቅቁ ቦታዎች አንደኛው ስፍራ ኾኖ ታገኙታላችሁ። የመኪና አደጋ ደርሶበት ፊቱ የተበላሸ፣ በኦክስጅን የሚተነፍሱ ህጻናት፣ ሽንት መቋጠር አቅቷቸው በቱቦ የሚሸኑ፣ ምጥ የሚያስጨኻቸው ነፍሰ-ጡር ሴቶች.... ይህ ሁሉ የተዘበራረቅ ትዕይንት በአንድ ክፍል ያጋጥማችኋል።

ታድያ የመጀመሪያው ጥያቄ ሊፈጠርባችሁ የሚችለው “እንዴት ነው እዚህ ውስጥ የምቆየው?” የሚል ሀሳብ በመኾኑ- ከድንገተና ክፍሉ ለመውጣት ትዳዳላችሁ።

የጤና ባለሙያዎች ግን አይወጡም፣ ከታማሚውም አይርቁም። በተለይ ደግሞ ነርሶች.... ትኩረት ያልተሰጣቸው የሆስፒታል ማገሮች... ክብር የተነፈጋቸው። በሽተኛን ተከባክበው ጤነኛ እንዲሆን የሚያደርጉት....
ባሳለፍናቸው ሳምንታት የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ለጤና ባለሙያዎች ያደረገው የመድህን መስጠት ተግባር በእውነቱ ሊደነቅ ይገባዋል። በተለይ አሁን ባለንበት አስፈሪ ጊዜ፣ በሽታውን ከፊት ኾነው እየገጠሙ ያሉት የጤና ባለሙያዎች፤ ሙያቸው ለቫይረሱ ተጋላጭ አድርጓቸው ሳለ መድህን ሊገባላቸው እንደኾነ መስማቱ ያስደስታል።

በፊት ሀገራችንን ከወራሪዎች የጠበቁልን፣ ከተለያዩ የሀገራችን ክፍል የተሰባሰቡ አርበኞቻችን ነበሩ፤ የጊዜው ጠላታችን ኮሮናን የሚመክቱልን እንዲሁ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው ጤና ባለሞያዎች ናቸው።
በዚህ መከራ ውስጥ እያለፉ ላሉት ባለሙያዎች ግን ራሳቸውን እንዲጠብቁ የተደረገው ድጋፍ አናሳ ነው ለማለት እንወዳለን።

ምናልባት አንዳንድ ሆስፒታሎች ለሰራተኞቻቸው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፣ ጓንት ያቀርቡ ይኾናል። አብዛኛው የጤና ባለሙያ ግን በማህበራዊ ትስስር ወጥተው እንደሚናገሩት አቅርቦቱ በቂ አለመሆኑን ነው። ስንቶቻችሁስ ለሆስፒታል የተሰጠ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፣ ጓንት እና የመከላከያ ልብስ በጎን በኩል አውጥተው የሚሸጡ የሆስፒታል አስተዳደሮች እንዳሉ የምታውቁ? እንደ አሜሪካ ያሉ ሀገራት

በምድራቸው ከሚያርፍ አውሮፕላን ለኮሮና መከላከያ የሚሆኑ ቁሶችን እንደሚሰርቁ ሰምተን ትዝብታችንን ከፍ አደረገው እንጂ፣ እዚሁ ሀገራችን ውስጥም ለጤና ባለሙያ እና ድጋፍ ለሚሹ ሰዎች መድረስ ያለበት ንብረት እንደሚሸጥ ትዝብት አምዳችን ከተከታዮቿ የደረሳት መልእክት እንዲሁም በማኅበራዊ ትስስር ከሚተላለፉ ዘገባዎች ተረድታለች። በተቃራኒው የከፋ ዞን ሽማግሌዎች ኮሮናን ለሚዋጉት የጤና ባለሙያዎች የበግ እና ማር ስጦታ ማቅረባቸው ብዙኃኑን ያስደነቀ ድርጊት ነበር- ይቀጥል ለማለት እንወዳለን።

ሌላው በዚህ ከባድ ጊዜ ለጤና ባለሙያዎች ህመም የኾነባቸው ነገር የማኅበረሰቡ መዘናጋት ነው። አዎ ሰዉ ለኮሮና ያለውን ግንዛቤ ወደ ተግባር ከመቀየር ይልቅ ችላ ሲል ይስተዋላል። ቸልተኝነት ደግሞ በእጅጉ ዋጋ ያስከፍላል። የታማሚዎች ቁጥር መጨመር የስራ ጫና የሚጨምርባቸው የጤና ባለሙያዎች ላይ ነው።

ለሰዓታት ያለ እረፍት የሚሰሩ፣ የለበሱት የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ የሚያቆስላቸው፣ ቤተሰቦቻቸውን ማየት የሚናፍቃቸው... እነዚህን የጤና ባለሙያዎች ናቸው። ስለዚህ ቢያንስ ለእነሱ ብለን አንዘናጋ- እነሱ ለህይወታችን ከሚያስቡት በላይ እኛ ለራሳችን እናስብ።

በሚስቴን ዳርኳት ፊልም "አመንካቸው" ብሎ የሚናገረው አንደኛው ተዋናይ- ከጊዜያት ቆይታ በኋላ ያገኘው ጓደኛው "ካንሰር እንዳለበት ተነግሮኛል፤ ለመኖር አንድ ወር ብቻ ነው የቀረኝ" ሲል የተናገረው ነው። አዎ ንዝህላል የኾኑ የጤና ባለሙያዎች አሉ። ቃል ከገቡለት ህዝብ ይልቅ ኪሳቸውን ለማደለብ የሚሮጡም፤ በሙያቸው አደገኛ ስህተት የሚሰሩም አሉ።

ግን ሁሉም እንደዚያ አይደሉም.... ምቾታቸውን ትተው ህዝባቸውን በቅንነት የሚያገለግሉ ሞልተዋል፤ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ለታማሚዎቻቸው ደህንነት የሚጨነቁ እልፍ ናቸው። እነዚህን እንመናቸው፣ የሚናገሩትን ነገር ተግባራዊ እናድርግላቸው። የሚነግሩን ለራሳችን እንደሆነ አንዘንጋ፤ የመከላከያ መንገዶችን በአግባቡ እንጠቀም።
የጤና ባለሙያዎች የመሸረሻ ምክር--
" ዛሬም ተራራቁ ብለን የምንመክረው ራሳችሁን እንድታድኑ ነው።
እጃችሁን ታጠቡ የምንለው እናንተ ስትታመሙ ማየትን ስለማንወድ ነው።
ራሳችሁን ጠብቁ የምንለው በእናንተ መታመም ኀዘናችን ወደር ስለማይገኝለት ነው።
በየእምነቶቻችሁ ጸልዩ የምንለው ዛሬን ተሻግረን ነገ እንድንተያይ በማሰብ፤ ልናጣችሁ ስለማንፈልግ ነው"

********



**እንኳን ለ ሲዳማ ብሄር የዘመን መለወጫ ፊቼ ጨምበላላ በሰላም አደረሳችሁ፡**

Hawalle Sidaamu daga diru soorro Fichee Chambalaallate Ayyaanira keeruni iilishino'ne!!!

የሲዳማ ሽማግሌዎች  የበዓሉን ዕለት የሚወስኑት የመሬትን፣ የፀሐይን፣ የጨረቃንና የከዋክብትን ሥርዓት ዑደት በመመልከትና የእነዚህን አካላት ቅንጅት በማጥናት ነው።  ይህም ኢትዮጵያውያን ከሥነ-ፈለክ ጋር የነበረንን ጥንታዊ የዕውቀት ግንኙነት እና ጠበብቶች እንደነበርን ያመለክተናል።
እንኳን ከአሮጌው ወደ አዲሱ አመት በሰላም አሸጋገረን አሸጋገራቹ!

**መልካም በዓል!**
**Dancha Ayyaana ikko'ne.**




የተከበራችሁ እና የተወደዳችሁ  የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ቤተሰቦች እንደምንድን ናችሁ? .... እንደሚታወቀው ቅንድል ዲጂታል መጽሔት በቅጽ -2 ቁጥር 1 ላይ በልዩ አቀራረብ ከተካተቱት ውስጥ አንዱ የጥያቄ እና መልስ ውድድር ነው። በመሆኑም በቅጽ-2 ቁጥር 1 መጽሄታችን ውስጥ የተጠየቁት ጥያቄዎች ፣ የጥያቄዎቹ መልስ እና የጥያቄው አሸናፊዎች   ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ።

የነበሩት ጥያቄዎች :

1. የሁለተኛው አለም ጦርነት እንዲቀሰቀስ ምክንያት የሆነው ክስተት የቱ ነው?

ሀ) የብሪታንያ ጦርነት  ለ) የፖላንድ ወረራ  ሐ) የዱኪ ፈርድናድ መገደል  መ) ሁሉም መልስ

2. በኢትዮጵያ ታሪክ የመኪና መንጃ ፍቃድ ለመጀመሪያ ጊዜ ያወጣው ሰው ማን ይባላል?

3. በአፄ ቴዎድሮስ እና በአፄ ዮሐንስ መካከል የነገሱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ማን ይባሉ ነበር ? ለስንት አመትስ ኢትዮጲያን አስተዳደሩ ? የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ።

የጥያቄዎቹ መልስ

ጥያቄ ቁጥር 1፦ በተለያዩ የታሪክ መጽሃፍት እና በወቅቱ የነበሩ የዐይን እማኞች እንደመሰከሩት ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመር እና እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሰው በአዶልፍ ሂትለር የሚመራው የናዚ ጦር ፖላንድን መውረሩ ነበር። በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ ፊደል ‹‹ለ›› ነው።

ጥያቄ ቁጥር 2 ፦ በኢትዮጵያ ለመጀመርያ ጊዜ መኪና ያሽከረከሩ፣ መንጃ ፍቃድም ያላቸው ግለሰብ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ይባላሉ። ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በመሰንቆ ችሎታቸው፣ ዘለሰኛና መዲና ዜማዎችን በሸክላ ያስቀረፁ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሙዚቀኛ፣ ባለቅኔና በግጥም የሚታወቁ፤ ወላይታን ያስተዳደሩ፣ የልጅ እያሱ ባለሟል የነበሩ ፤ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አውቶሞቢል ነጂና ጠጋኝ ፣ የመንግስት ባለስልጣን ፖለቲከኛ እና ቀራፂ ነበሩ።

ጥያቄ ቁጥር 3፦ በ አፄ ቴዎድሮስ እና በ አፄ ዮሐንስ መካከል ለ 3 አመት የነገሱት ንጉሥ  አፄ ተክለጊዮርጊስ ሲሆኑ ዘመኑም እ.ኤ.አ 11 June 1868- 11July 1871 ነበር።

#ይመልሱ ይሸለሙ

**የቅን-ድል ዲጂታል መጽሔት የቅጽ-2 ቁጥር -1 የሽልማት ጥያቄ አሸናፊዎች።**

1. ሳሙኤል በየነ (ከአዲስ አበባ-
2. ዶ/ር ሀብታሙ መሰለ (ከ ወልድያ)

በአጠቃላይ በአሸላሚ ጥያቄዎቹ ላይ ተሳታፊ የነበራችሁ ሰዎች እጅግ ብዙ ብትሆኑም ጥቂቶቻችሁን ከዚህ በታች ስማችሁን አስቀምጠናል።

-ሙላለም አበበ (ከደብረ ብርሀን)
-መሀሙድ አህመድ (ከደሴ)
-ፋይሰል አብዱላዚህ (ከአግፋሪ ኮሌጅ)
-ኢብራሂም (ከሰበታ)
-በሀይሉ ሰቦቃ (ከአዲስ አበባ)

**የቅንድል መፅሔት ቅፅ 2 ቁጥር-2 የልዩ ሽልማት ጥያቄዎች**

የቅንድል ዲጂታል መፅሔት የሀገራችን ብሎም የአለማችንን ታሪክ እንዲሁም የተለያዩ አንባቢያንን ሊያስተምሩ እና ሊያዝናኑ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ሽልማቶችን ለአንባቢያን ለመስጠት ተዘጋጅቷል ። በመሆኑም የዚህ ዕትም ጥያቄዎች እና የሽልማት ህጎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

1. የአባይን መነሻ ያጠናው ስኮትላንዳዊው ጀምስ ብሩስ በኢትዮጲያ በቆየባቸው አመታት ይጠራበት የነበረው ሀገርኛ ስም ማን ይባል ነበር?
2. በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የፓርላማ ተመራጭ ፣የትምህርት ቤት ዳይሬክተር እና የመጀመሪያዋ የውጭ ሀገር  የትምህርት ዕድል ያገኘች ግለሰብ ማን ይባላሉ?
3. ኤርትራ ስንተኛዋ የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገር ነች?

**ማስታወሻ** ፦ አሸናፊ የሚሆኑት መላሾች   መፅሔቱ ከወጣበት ሰዓት ጀምሮ መልሱን ከዚህ በታች ከተጠቀሱት የስልክ ቁጥሮች ውስጥ በአንዱ መልሶቻቸውን በሞባይል መልዕክት (SMS) ቀድመው ለላኩ ሁለት መላሾች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል።

❖የጥያቄው መልስ እና የጥያቄው መላሾች በቀጣይ በምትወጣው ቅፅ2-ቁጥር 3 መፅሔት ላይ ይጠብቁን!
❖መላሾች መልሶቻችሁን ስትልኩ ስም እና የመኖርያ አድራሻዎቻችሁን አያይዛችሁ መላካችሁን እንዳትረሱ።
❖መላሾች ሽልማታችሁ የሚሆነው ብታነቧቸው  ትማሩበታላችሁ፣ ትጠቀሙበታላችሁ ብለን የምናስባቸውን የታሪክ መፅሐፍት ይሆናል።

✆+251904064276
✆+251924140293
✆+251912178520

★መልካም እድል!★

# ኮሮና የፈጣሪ ቁጣ ወይስ ከበሽታዎች አንዱ?

## እየጨመረ መሄዱስ ተጨማሪ ፀሎት ወይስ ተጨማሪ ጥንቃቄ አስፈልጎን ይሆን?

በ ገላና ጥጉ

ይሄንን ጥያቄ እንድጠይቅ ያደረገኝ ነገር የአንድ ሰው ንግግር ነው፣ የኮሮና ተጠቂዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ያስጨነቀው አንድ ወንድም ለወዳጁ "ኮሮናም እየጨመረ ነው። እኛም ቁጣው እስኪመለስ ጾሎትን እንጨምር'' ሲል ወዲያዉ ወደ አእምሮዬ እንዲህ የሚል ጥያቄ መጣ '' የጎረቤት አገር የሆነችውን ኤርትራን ጨምሮ ሌሎችም አገራት እንደ ሞሪሽየስ፣ ኒውዘርላንድ እና የመሳሳሉት አገራት፣ ምንም እንኳ በሽታውን ሙሉ በሙሉ ባይቆጣጠሩም ፣ አዲስ ታማሚ እንደሌለ እና በሽታውን እየተቆጣጠሩ እንዳሉ ሲናገሩ 'ታድያ ኮሮና የፈጣሪ ቁጣ ከሆነ የእነዚህ አገራት ደግነት እና ፈጣሪን መፍራታቸዉ እንዲሁም የፀሎት ሕይወታቸዉ ከሌሎች ሃገራት በልጦ ነው ወይ? የፈጣሪንስ ቁጣ እኛ የሰዉ ልጆች መቆጣጠር እንችላለን?'' የሚል ጥያቄ በአዕምሮዬ ውስጥ ተደረደሩ።

እንደሚታወቃዉ እኛ ኢትዮጵያዊያን በፈጣሪ የምናምን ፣ ብዙ ጊዜ ሲባል እንደምንሰማው ከ97% በላይ አማኞች ነን። ሁላችንም ማለት በሚቻልበት መልኩ እየጸለይንም እንገኛለን።
መቼም ጸሎታችን ከኮሮና ጋር የሚሄድ ማለትም ኮሮና ሲጨምር የሚጨመር፣ ሲቀንስ የሚቀነስ ሳይሆን ዘወትር የሚቀጥል ሆኖ ይበልጡኑ ህዝባችን ከመቼውም ጊዜው በላይ እንዲያስተውል ማለትም ፈጣሪ የሰጠውን አዕምሮ በሚገባ እንዲጠቀምበት፣ ፈጣሪ ማስተዋልን እንዲያበዛ፣ ነገሩ ከአቅማችን በላይ በመሆኑ ፈጣሪ አቅም እና ፅናት እንዲሁም ጥበብ እንዲያበዛልን ፀሎታችን በዚህ መረዳት መቀጠል አለበት ባይ ነኝ።

በመሆኑም እኔ በግሌ ኮሮና የፈጣሪ ቁጣ ነዉ ብዬ አላምንም። ለዚህም ማሳያ ሊሆን የሚችል አንድ ሁለት ምክንያቶችን ላንሳ

1. የፈጣሪን ቁጣን ንፅህናችንን በመጠበቅ እና አፍ እና አፍንጫ በመሸፈን መቆጣጠር አንችልም! ይህ ግልፅ ነው። ፈጣሪ ተቆጥቶ ቢሆን በፊት መሸፈኛ ጭንብል በፍፁም አታመልጠውም።

2. ፈጣሪ ሲቀጣ በጅምላ አይደለም፣ ማለትም ሊቀጣ ያለውን በመለየት እንጂ በጅምላ ሁሉንም አይቀጣም።

ይሁን እና የሰው ልጆች ፈጣሪ የሰጣቸውን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው በራሳቸዉ ስህተት ያመጡት ነው ብዬ አምናለሁ። የግልም ሆነ የአከባቢያችንን ንፅህና በመጠበቅ ጤናችንን መጠበቅ እንዳለብን እያወቅን ሳንተገብር ብንቀር እና ብንታመም ፈጣሪን ተጠያቂ ማድረግ ራሱ ኃጥያት ነው። ስለ ሆነም በራሳችን ስህተት እና እንዝላልነት ያመጣነውን "የፈጣሪ ቁጣ ነው" እያልን በፈጣሪ ሳናላክክ እና መልካሙን አምላክ ተጠያቂ ባለማድረግ ፤ እሱ በሰጠን አዕምሮ በማሰብ እና በማስተዋል ራሳችንን ከዚህ አስከፊ በሽታ እንድንጠብቅ አደራ እያልኩ ''ግመሌንም አስራለሁ፤ ፈጣሪንም አምናለሁ'' የሚለውን ብሂል በማስታወስ አበቃሁ። ሻሎም!!!

ቸር እንሰንብት!!!

**የቤተሰብ ወግ**
**የቤተሰብ ወግ አምድ እጅግ ለምናከበራቸው የመፅሔታችን አንባቢያን እና የቅን ቤተሰቦች የሀሳብ ዕልፍኝ እንድትሆን በማሳብ በተለያዩ የማህበራዊ ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሀሳቦችን እና የህይወት ተሞክሮዎችን ለአንባቢያን የሚያሰፍሩበት ገፅ ነው።**

**ፅሁፎቻችሁን ስትልኩልን የሀገራችንን ባህል፣ወግ እና ስርአት የማይጣረስ ፣ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት መርሆዎችን የተከተለ ፣ ሰዎችን ሊያስተምር የሚችል ፣ የሆሄ መጠን(FONT SIZE) 12 እንዲሁም የሆሄ ብዛት ከ500 ያልበለጠ መሆኑን አረጋግጣችሁ ከታች ባለው አድራሻ ብትልኩልን መልሰን ወደ እናንተ እናደርሳለን።**

KDIGITALMAGAZINE@GMAIL.COM

ዞስ ካሌስ
አካውንታንት(Bsc)
zoskales27@gmail.com



# እውን ኮሮና የላብራቶሪ ስሪት ነው?

ኮሮና አለም ላይ መንሰራፋት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፣ ከበሽታው መስፋፋት ባልተናነሰ መልኩ፣ ኮሮና የላብራቶሪ ስሪት ነው፣ አይደለም የሚለው አጨቃጫቂ ጉዳይ ሆኖ ሰንብቷል። ምንም እንኳ አሁን ረገብ ያለ ቢመስልም፣ መጀመሪያ አካባቢ የቻይናና የኢራን ባለስልጣናት፣ እንዴ አሜሪካን፣ እንዴ እስራኤልን ሲወቅሱ፤ አሁን ደግሞ በተገላቢጦሽ አሜሪካ ቻይናንን እየወቀሰች ትገኛለች። አሜሪካ ተጠያቂነቱን ወደቻይና ማዞር ብቻ ሳይሆን ካሳ እንድትከፍል ተፅዕኖ ለማሳደር እየሞከረች ነው። የቻይና ምላሽ ለዘብ ያለ ቢሆንም፣ የሁለቱ ንትርክ ከበሽታው በስተጀርባ ብዙ ፖለቲካዊ ነገሮችን ያዘለ እንደሚሆን የሚያጠያይቅ አይደለም።

አሁን ላይ በአለም ብዙ ሚሊዮን የኮሮና ተጠቂዎች ሲኖሩ፣ ባልተጠበቀ ሁኔታ ብዙዎቹ ሲሞቱ፣ አብዛኞቹም አገግመዋል። በተለያየ ግዜ የሚወጡት የዜና ምንጮች ኮሮና ቫይረስ SARS-COV-2 በሚባል ሳይንሳዊ ስሙ ሚታወቅ ሆኖ ከቻይና ውሀን ላብራቶሪ አምልጦ የወጣ ነው ሚሉ መላምቶች በአብዛኛው ያነሳሉ። ለዚህም ይመስላል በአፕሪል 16 የአሜሪካ መንግስት ይፋዊ በሆነ መግለጫው፣ ኮሮና የላብራቶሪ ስሪት መሆኑን ገልፆ፣ ለበለጠ ጠንካራ የመረጃ ባለሞያዎቻቸው እየሰሩበት እንዳሉና እርግጥ ሆኖ ከተገኘ፣ ቻይና ብዙ ማዕቀቦች እንደሚጠብቃት መጠቆማቸውን፣ ብዙ የዜና አውታሮች ተቀባብለውት ነበር። በእርግጥ ብዙ እውቅ ሳይንቲስቶች ባይስማሙበትም፣ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ፣ ቻይናን ተጠያቂ አድርገው፣ የእጇንም እንደሚሰጧት ሲዝቱና፣ ጠንከር ያሉ ትችቶችን ሲያዘንቡባት ተስተውለዋል። እውነት እነሱ እንደሚሉት ኮሮና የላብራቶሪ ስሪት ነው? ከዚህ አንፃር የጤና ባለሞያዎችስ ምን ይላሉ?

ብዙ ነገር ይባል እንጂ እውቅ የሆኑ የሳይንቲስቶች ስብስብ ነገሩን ውድቅ እያደረጉ ይገኛሉ። በዚህም ኮቪድ 19 በመውሰድ ከሱ በፊት የሰውን ልጅ ሲያጠቁ የነበሩትን SARS, MERS, NL63, OL43, 229Eና አጠቃላይ 7 ሚሆኑ በሽታዎች ላይ ጥናት አካሂደዋል፣ ይሁንና SARS-COV-2 በላብራቶሪ ውስጥ አለመፈብረኩን አስቀምጠዋል። ተባባሪ ፕሮፌሰር ክርስትያን አንደርሰን (የስነተዋሲያንና የበሽታ መቋቋም ተመራማሪ) እንደሚናገሩት፣ የኮሮናን ጅን ብንመለከት በውጨኛው በኩል ሹል ሆነው ወጣ ብለው ሚገኙት የፕሮቲን ሴሎች ይገኛሉ፣ እነዚህ የፕሮቲን ሴሎች በመጠቀም፣ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ ይጠቀምበታል። የጅን ቅድመ ሁኔታውን ብንመለከት፣ ኮሮና ሁለት ሹል የፕሮቲን መልክ ሲኖረው፣ አንደኛው ሴል እንግዳው ሴል ውስጥ፣ ሲጣበቅ ቫይረሱን ተሸካሚ ሁለተኛው ቫይረስ ወደ ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል።

ታድያ ተመራማሪዎች እንደሚሉት አንደኛው የኮሮና ሴል ትኩረት ሚያደርገው በውጪኛው የሰው ልጅ ተቀባይ ሴል ላይ ነው፣ ይሄም ACE2 ይባለል። ውጨኛው ሴል ተቀባይ ፣ከደም ዝውውር ጋር ቀጥተኛ ተሳትፎ ስላለው፣ ወደ ሌላኛው የሰው ልጅ ሴል ጋር ለመድረስ ሚያደርገውን ጥረት የተሳካ ያደርገዋል፣ ታድያ በኮሮና ጫፍ ላይ ሚገኙት እነዚህ አስተላላፊ ፕሮቲን እዘል ሴሎች፣ ተፈጥሯዊ ምርጫ እንጂ በጄኔቲክ ኢንጂነሪንግ እንዳልመጡ ያሳያል። ይሄም ለምን SARS-COV-2 ከ SARS ጋር ትልቅ ቅርርብ እንዳለው አመልካች ነው፣ SARS አለም ላይ ወደ 20 አመታት ቆይቷል፣ SARS ከSARS-COV-2 የተለያዩ እንደሆኑ፣ ሳይንቲስቶችም ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። SARS-COV-2 በጄኔቲክ ኢንጂነሪንግ ከSARS መለወጡን ሚያሳይ ምንም ማስረጃ እንዳላገኙም ይናገራሉ፣ በጄኔቲክ ኢንጂነሪንግ እንለውጠው ቢሉ እንኳ፣ የተለውጠ ባህሪውን መምረጥ አይችሉም፣ ምክንያቱም እነሱ በሚያስቡት መንገድ መለወጥ ማይታሰብ ስለሆነ። ተፈጥሮ ከሳይንስ በላይ ብልጥ ነች።

ሌላው ከላብራቶሪ ያመለጠ በሽታ ነው ሚለውን ፅንስ ሀሳብ ውድቅ ሚያደርገው፣ ኮሮና የተዋቀረበት ሞሎኪውላር ይዘት ተለምዷዊ የሰውን ልጅ ከሚያጠቁ በሽታዎች ይልቅ የሌሊት ወፎችን ከሚያጠቁ ቫይረሶች ጋር ተመሳሳይነት በመኖሩ ነው። የሰውን ልጅም እንደሚጎዳም በደንብ ሚታወቅ ነው፣ አንድ ሰው እንደ ኮሮና አይነት በሽታ በላብራቶሪ ልፍጠር ቢል፣ በመጀመሪያ በሽታው ታውቆ ከዛ በኋላ ነው እንዲበዛ የሚደረገው እንጂ በባዶ ከመሬት ተነስቶ የሚሰራ በሽታ እንዳልሆነ ሳይንሲስቶች ያረጋግጣሉ፣ ይሄ ማለት ኮቪድ 19 ለመስራት የተቀመጠ ቀመር እንደሌለ ያረጋግጣሉ። በእርግጥ ከኮሮና ጋ በተያያዘ ብዙ ጥናትና ምርምሮች አሁን ድረስ እየተካሄዱ ቢሆኑም፣ ሁነኛ የበሽታውን ባህሪ አለመታወቅ፣ ለተመራማሪዎች አዳጋች አድርጎታል። ይሁንና የጀርመን፣ አሜሪካ፣ ጃፓንና ቻይና ልሂቃን አመርቂ ውጤቶችን እያስገኙ ይገኛሉ፣ የተለያያ ድምዳሜ ላይ የደረሱበት ሁኔታም አለ።

እሺ ኮሮና ቫይረስ በላብራቶሪ ውስጥ አልተሰራም ምንል ከሆነ፣ እና ከየት መጣ?

እዚህ ጋር ሳይንቲስቶች ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን ያነሳሉ፣ በአንደኛው ረድፍ ሚነሱት ሀሳቦች፣ እነዚህ የኮሮና ዝርያዎች፣ ከዚህ በፊት የሰውን ልጅ ሲያጠቁ ከነበሩ ቀድሞ ቫይረሶች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፣ ይሄም ቀጥታ ከሌሎች እንስሳቶች የመጣና ወደ ሌሎች እንስሳት ከዛም ወደ ሰዎች የተላለፈ ነው የሚል መላምት ያስቀምጣሉ። ለምሳሌ ከለሊት ወፍ፣ በዚህም የሰውን ልጅ ማጥቃት የሚችሉ ቫይረሶች ተከስተዋል የሚል ግምትን እንደመከራከሪያነት ያነሳሉ፣ ሌላኛው በሳይንቲስቶች የተሰጠ መላምት፣ ቫይረሱ ቀጥታ ከእንስሳት ወደ ሰው ልጅ ካለፈ በኋላ በተቀባዩ የሰውነት ክፍል ውስጥ ጎልብቶ፣ ወደ ሌላ አደገኛ ደረጃ አድጎ፣ በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው በመተላለፍ የቻለ በሽታ ነው ሚለውን ጥናት ያቀርባሉ።

አሁን ከላይ የተጠቀሱት ጥናታዊ መላምቶች፣ የወደፊት የበሽታዉን ተደራሽነት ለማወቅ ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ይጠቅሳሉ፣ መጀመሪያ ላይ እንደተጠቀሰው ቀጥታ ከሌሎች እንስሳት ወደ ሰው ልጅ የተላለፍ ከሆነ፣ በሽታው እንደወረርሽን ድጋሚ መነሳት ስለሚችል ከአለም ላይ መጥፋት አይችልም፤ በሰዎች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በእንስሳት ውስጥም ስለሚሽከረከር፣ በተደጋጋሚ ወደ ሰው ልጅ ለመተላለፍ ብዙ እድል አለው፣ አይቀሬም ነው። ነገር ግን ወደ ሰው ልጅ ውስጥ ከተላለፈ በኋላ ራሱን አሳድጎ፣ አጎልብቶና ፀባዩን ቀይሮ ወደ ሌሎች የሰው ልጆች ሚተላለፍ ከሆነ፣ እንዲህ አይነት የበሽታ አይነቶች ድጋሜ እንደወረርሽኝ የመነሳት መንስኤያቸው፣ ትንሽ ስለሚሆን አስጊ አይደሉም፣ የሚሉ ናቸው።

# ቅንድል መፅሔት

ቅንነት ድል ያደርጋል!















## በፌስቡክና በቴሌግራም ቤተሰብ ይሁኑ!

TELEGRAM @KENDELM | FACEBOOK ቅንድል ዲጂታል መፅሔት